# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሰኞ 84ኛ ዓመት ቁጥር 104 ታኅሣሥ 14 ቀን 2017 ዓ.ም ዋጋ 34.50 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!









ፎቶ፡- በጠቅላይ ሚኒስትር ቢሮ

# "በባሕር በር ጉዳይ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ እና መንግሥት ከፈረንሳይ እና ከፕሬዚዳንቷ የሚጨበጥ ውጤት ይጠብቃሉ"

## - ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ ፦ በባሕር በር ጉዳይ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ እና መንግሥት ከፈረንሳይ እና ፕሬዚዳንት ኢማኑኤል ማክሮን የሚጨበጥ ውጤት እንደሚጠብቅ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) አመለከቱ። ፈረንሳይም ባላት አቅም ማድረግ የምትችለውን እንደምታደርግ ፕሬዚዳንት ኢማኑኤል ማክሮን አስታወቁ።

የፈረንሳዩ ፕሬዚዳንት ኢማኑኤል ማክሮን የኢትዮጵያ የአንድ ቀን ይፋዊ ጉብኝት አስመልክተው ትናንት መሪዎቹ በጋራ በሰጡት መግለጫ፤ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ፤ ኢትዮጵያ በሰላማዊ መንገድ የባሕር በር በማግኘት ፍላጎቷ ዙሪያ ከፕሬዚዳንቱ ጋር በዝርዝር መወያየታቸውን አስታውቀዋል።

130 ሚሊዮን ሕዝብ ይዛ፣ ፈጣን ኢኮኖሚ እያስመዘገበች ያለችው ኢትዮጵያ በዓለም ሕግ ፣ በሰላማዊ እና በዲፕሎማሲያዊ መንገድ የባሕር በር ለማግኘት ለምታደርገው ጥረት ስኬት እንደ ፈረንሳይ ያሉ ወዳጅ ሀገራት ጠንካራ ድጋፍ ያስፈልጋታል፤ ይህንንም የድጋፍ ጥያቄያችንን ፕሬዚዳንት ኢማኑኤል በአክብሮት ተቀብለውታል ብለዋል።

ፕሬዚዳንት ማክሮን ጥያቄውን ስለመቀበላቸው ከፍ ያለ ምስጋና ያቀረቡት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ፤ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ እና መንግሥት ከፈረንሳይ እና ፕሬዚዳንት ኢማኑኤል ማክሮን በባሕር በር ጉዳይ የሚጨበጥ ውጤት የሚጠብቁ ስለመሆኑም ጠቁመዋል።

ለታላቁ ቤተመንግሥት እድሳት የአንበሳውን ድርሻ የሚወስዱት ፕሬዚዳንት ኢማኑኤል ማክሮን መሆናቸውን

"በባሕር በር ጉዳይ ... ወደ ገጽ 3 ዞሯል

## ኢትዮጵያ የጋራ በሆኑ ጉዳዮች ላይ አብረን እንሥራ፤ እንተባበር እያለች መሆኑ ተገለጸ

ምሕረት ሞገስ

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ ለጎረቤት ሀገራት በመደመር አስተሳሰብ አንድ ላይ እንሥራ የሚል ሃሳብ እያቀረበች መሆኑን በውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩት የአውሮፓና የአሜሪካ ጉዳዮች ዳይሬክተር እና የኢትዮጵያ ፖለቲካ ተንታኝ ዳርእስከዳር ታዬ (ዶ/ር) አስታወቁ፡፡

ዳርእስከዳር ታዬ (ዶ/ር) ከአዲስ ዘመን ጋዜጣ ዝግጅት ጋር ባደረጉት ቃለምልልስ ላይ እንደተናገሩት፤ በጎረቤት ሀገራት መካከል ቀደም ሲል የመጠራጠርና በጠላትነት የመተያየት ሁኔታ ነበር፡፡ ኢትዮጵያ ይህንን ሁኔታ በመቀየር የጋራ በሆኑ ጉዳዮች ላይ አብረን እንሥራ፤ እንተባበር እያለች ትገኛለች።

ኢትዮጵያ ከጎረቤት ሀገራት ጋር የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት እና የማንነት ተመሳሳይነት አላት፡፡ ይህን ግንኙነት ይበልጥ ለማጠናከር በጋራ መሥራት የሚቻልባቸው ነገሮች ላይ አብሮ ማጥናት እና መሥራት እንደምትፈልግ አመልክተዋል፡፡ ከሌሎች ተመሳሳይ ፍላጎት እና ምላሽ ቢገኝ ጥሩ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

እንደእርሳቸው ገለፃ፤ አሁን የኢትዮጵያ መንግሥት በጋራ መሥራት የሚቻልባቸው ነገሮች ላይ በተለይም ሰላም ከማምጣት አንፃር ብዙ ሥራዎችን እየሠራ ይገኛል፡፡ አላስፈላጊ ሲሆንም ራስን የማግለል እርምጃ ይወሰዳል፡፡

ኢትዮጵያ የጋራ- ... ወደ ገጽ 2 ዞሯል



## "ውጤታማና የላቀ የፍትሕና የዳኝነት አገልግሎትን ለመስጠት ሀገር አቀፍ የሪፎርም ሥራዎች እየተሠሩ ነው"

የፍትሕ ሚኒስትር ዴኤታ ኤርሚያስ የማነብርሃን (ዶ/ር)

ገጽ 3



# የተዘነጉ ቅርሶችንና ወረቶችን- ሀብት ወደ ማፍራት ያሸጋገረ አዲስ ዕይታ

ኢያሱ መሰለ



የሀገር በቀል ኢኮኖሚው ማሻሻያ ምሰሶ ናቸው ተብለው ከተለዩት አንዱ ቱሪዝም ነው። የቱሪዝም ኢንዱስትሪው በሀገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ የሚኖረውን አስተዋጽኦ ለማሳደግ የቱሪስት መዳረሻዎችን የማስፋት፣ ቅርሶችን የመጠገንና የማደስ ፣ ከተሞችን የማዘመን፣ ታሪካዊ ቦታዎችን እና ታሪክ ገላጭ ቁሳቁስን ለቱሪስቶች ክፍት በማድረግ ወረትን ወደ ሀብት የመቀየር ሥራ እየተሠራ ነው።

ታላቁ ቤተ-መንግሥት፣ የጂማ አባጅፋር ቤተ-መንግሥት ታድሰውና ተውበው ለጎብኚዎች ክፍት መደረጋቸው የሚታወስ ነው። ከሰሞኑም የኢዮቤልዩ ቤተ-መንግሥት ሙዚየም ተጠናቆ ለጎብኚዎች ክፍት ሊደረግ መሆኑ እየተነገረ ነው። የጎንደር የፋሲል ግንብ፣ የላልይበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት ዕድሳት እየተካሄደ ሲሆን፤ የአክሱም ሐውልትና ሌሎችም እድሳት ሊደረግላቸው እንደሆነ ታውቋል። የቱሪስት ጸጋን ወደ ሀብት ለመቀየር እየተደረገ ያለውን ንቅናቄ የዘርፉ ሙያተኞች እንዴት ይገልጹታል?

በኢትዮጵያ ቅርስ ባለሥልጣን የቅርስ ምርምር መሪ ሥራ አስፈጻሚ ዮናስ ይልማ (ዶ/ር) እንደሚገልጹት፤ ማንኛውም ሀገር ኢኮኖሚያዊ እድገቱን የሚያስቀጥለው ባለው ሀብት ላይ ተመስርቶ ነው፤ ኢትዮጵያ ከፍተኛ የቅርስ ሀብት ያላት ሀገር ነች፤ ይህን ከፍተኛ ሀብት በአግባቡ ጥቅም ላይ ማዋል ቢቻል ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነትን ማሳደግ ይቻላል።

ለዘመናት ጥቅም መስጠት ሲገባቸው ከጎብኚዎች እይታ ተሰውረው የቆዩ ቅርሶች በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች አሉ። ቱሪዝም በኢኮኖሚ ውስጥ ያለውን ሚና እንዲወጣ ሲታሰብ እነዚህን ሀብቶች ጥቅም ላይ ማዋል የግድ ይላል። ከቅርሶቹ ሀገር ማግኘት ያለባትን ጥቅም እንድታገኝ መደረጉም ተገቢነት ያለው ነው። ቅርሶች ባህላዊ፣ ኪነ-ጥበባዊ፣ ታሪካዊና ትምህርታዊ ፋይዳቸውም ከፍተኛ ነው ይላሉ።

ቅርሶችን አሰባስቦ የሚይዝ ሙዚየም ተገነባ ማለት ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ደህንነታቸው ተጠበቀ ማለት ነው። ከትውልድ ወደ ትውልድ የመተላለፍ ዋስትናም ያገኛሉ። በተለያዩ ቤተ መንግሥቶች የሚገኙ ቅርሶችን ለጎብኚዎች ክፍት ማድረጉ የውጭ ብቻ ሳይሆን የሀገር ውስጥ ጎብኚዎች ቁጥር እንዲጨምር የሚያደርግ እንደሆነ ያስረዳሉ።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የቅርሳ ቅርስና ቤተመጻሕፍት ወመዘክር ቱሪዝም መምሪያ ዋና ኃላፊ መላከ ሰላም ቀሲስ ዳዊት ያሬድ በበኩላቸው፤ ቅርሶች ትናንት የነበሩ ትውልዶች ምን ነበሩ? የሀገሪቱና የሕዝቦቿ የእድገትና የስልጣኔ ደረጃ ምን ላይ ደርሶ ነበር? ታሪኳ ምንድን ነው? የሚለውን ቁልጭ አድርገው የሚያስረዱ ናቸው ይላሉ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን እንደ ሀገር በዩኔስኮ የተመዘገቡ ቅርሶችን በባለቤትነት ታስተዳድራለች። ይሁንና የምታስተዳድራቸው ቅርሶች ከአንድ ተቋም አልፈው ፣ የሀገር ፣ ከሀገርም አልፈው የዓለም ሀብት ናቸው። ቅርሶች የእገሌ ወይም የእገሌ የሚባሉ አይደሉም፤ የሚወክሉት ፣የሚገልጡትና የሚያሳዩት ሀገርን እና ሕዝብን ነው፤ ቅርሶችን የማሰባሰብና የማደስ ሥራ ከሚሠራ ጋር ሁሉ በገንዘብ፣ በሙያ ፣ በሃሳብና በጉልበትም ጭምር መተባበር ያስፈልጋል ነው ያሉት።

መንግሥት የቱሪዝም ዘርፉን አንድ የኢኮኖሚ ምንጭ አድርጎ እየሠራ ከመሆኑ አንጻር ቅርሶችን በማደስ እና በመንከባከብ ገቢን ለማሳደግ የሚያደርገው ጥረት የሚደገፍ ነው ይላሉ።

ቅርሶች የሀገር ውስጥንም ይሁን የውጭ ሀገር ጎብኚዎችን በመሳብ በኢኮኖሚው ዕድገት ላይ የራሳቸውን አስተዋጽኦ ያበረክታሉ። ለምሳሌ እዮቤልዩ ቤተ-መንግሥት ከአሁን ቀደም ለቱሪስት ክፍት ባለመደረጉ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ሲሰጥ አልነበረም። አሁን ለቱሪዝም ዘርፉ ከተሰጠው ትኩረት አንጻር በውስጡ ያለውን ሀብት በአንድ አሰባስቦ ለጎብኚዎች ክፍት ለማድረግ መዘጋጀቱ የገቢ አቅም ከመፍጠርም በላይ በቅርሶች ጥገና ፣ በሙዚየም ማደራጀት እና በአስጎብኚዎች ዘርፍ ለበርካታ ሰዎች የሥራ እድል የሚፈጥር ነው የሚሉት ደግሞ አቶ ሀብታሙ አብርሃ በኢትዮጵያ ቅርስ ባለስልጣን የቅርስ ጥበቃና ልማት መሪ ሥራ አስፈጻሚ ናቸው።

የቱሪዝም ኢንዱስትሪ ተጠቃሚ የሚያደርገው የተወሰኑ አካላትን ብቻ ሳይሆን ከትልልቅ ድርጅቶች እስከ ግለሰቦች ድረስ ያሉትን በሙሉ ነው፤ የእነዚህ ሁሉ ድምር ውጤት እንደሀገር ኢኮኖሚውን ያነቃቃል። አንድ ቅርስ በዓለም ቅርስነት የሚመዘገበው ለዕይታ ሲቀርብ ነው። በዘርፉ ስምና ዝናን ካተረፉ ሀገራት ጋር በመተባበር ቅርሶችን በማደስና በመጠበቅ በዓለም ዘንድ ጎልተው እንዲታዩ ማድረግ ትልቅ ጥቅም እንዳለው ያመለክታሉ።

ከዚህ አንጻር ፈረንሳይ ከፋይናንስና ከሙያዊ ድጋፍ፣ ከቴክኖሎጂ ሽግግርና ከልምድ ልውውጥ አንጻር ለኢትዮጵያ በቅርሶች ዕድሳት እያደረገች ያለው ድጋፍና አስተዋጽኦ ትልቅ ዋጋ የሚሰጠው ነው ይላሉ ዶ/ር ዮናስ።

አቶ ሀብታሙ ይህንኑ ሃሳብ ሲያጠናክሩ፤ ቅርሶች የአንድ ሀገር ብቻ ሳይሆኑ የዓለም ሀብት ናቸው፤ ለአንድ ሀገር ሕዝብና መንግሥት የሚተው ጉዳይ ስላልሆነም ነው ዩኔስኮ እውቅና እየሰጠ ጥበቃ የሚያደርግላቸው ይላሉ፤

የፈረንሳይ መንግሥት ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ቅርሶችን በማደስ እና በመንከባከብ ተባባሪ መሆኑ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የሠሩት የዲፕሎማሲ ውጤት እንደሆነ ቢታወቅም፤ እንደ ሀገር ኢትዮጵያ ብቻዋን ማከናወን የማትችለውን የጥገና ሥራ የፈረንሳይ መንግሥት ማገዝ የቻለው፤ ቅርሶች ዓለም አቀፍ ሀብት በመሆናቸውም ጭምር እንደሆነ ያስረዳሉ። እገዛው ከፋይናንስ አቅም ጋር ብቻ ሳይሆን ከሙያ አንጻርም በመሆኑ ቅርሶችን በጥንቃቄ ለማደስ ትልቅ እድል እንደሆነ ያብራራሉ።

አሠራርን የሚያቀሉ ቴክኖሎጂዎች ባሉበት በዚህ ዘመን ያልተሠሩ ሥራዎች በጥንቱ ዘመን ተሠርተዋል የሚሉት መላከ ሰላም ቀሲስ ዳዊት በበኩላቸው፤ በላሊበላ ፍልፍል አቢያተ ክርስቲያናት ከአንድ ወጥ ድንጋይ ሥነ- ሕንፃና ሥነ-ውበት ተጣምረው የታዩበት፤ ዛሬም ድረስ የሚያስደምም ድንቅ ሥራ እንደተሠራ ያስረዳሉ።

ይህ ደግሞ አባቶቻችን ከብዙ ዓመት በፊት ዛሬን አሻግረው የተመለከቱ መሆኑን የሚያሳይ ነው ይላሉ።ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የፈረንሳይ መንግሥትን በማነጋገር ቅርሶች እንዲታደሱ የሚያደርጉትን ጥረት አድንቀው፤ በላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት ላይ ጥገና እንዲደረግ ማድረጋቸውም ተገቢነት ያለው ስለመሆኑ ያስረዳሉ።

አቶ ሀብታሙ፤ ቅርሶች ያለፈውን የአሁኑንና የመጪውን ትውልድ ማስተሳሰር የሚችል ጥልቅ እና እምቅ የሆነ ጥበባዊ ፋይዳ ያላቸው ናቸው ይላሉ። እንደ ላልይበላ ያለውን ድንቅ የእደጥበብ ውጤት ሀገሬው ብቻ ሳይሆን ዓለምም በስስት የሚመለከተው ነው። ቅርሶችን መጠበቅ በአግባቡ ማደራጀትና ለቱሪስቶች ክፍት ማድረጉ ኢኮኖሚያዊ ትርፍን የሚያስገኝ ከመሆኑም ባሻገር የአንድን ሀገር የስልጣኔ ደረጃ፣ የአኗኗር ባህል እና ታሪክ የሚያስረዳም እንደሆነ አብራርተዋል።

በኢዮቤልዩ ቤተ-መንግሥት የሚገኙ ቅርሶች ታድሰውና ለጎብኚዎች በሚስቡ መልኩ ክፍት የሚደረጉ መሆኑንም የሀገሪቱን ታሪክ ለመረዳት የሚያስችል እና ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ያለው እንደሆነ ይገልጻሉ።

ሁሉም ሰራሽ ቅርሶች ታሪካዊ ይዘታቸውን በጠበቀ መልኩ አድሶና ተንከባክቦ ወደ ሀብት ለመቀየር የሚደረገው ጥረት ነገ ኢኮኖሚያዊ ፍሬውን እንድናጣጥም ያደርገናል ነው ያሉት ምሁራኑ።

# ያልተገባ የዋጋ ጭማሪ በሚያደርጉ ነጋዴዎች ላይ ግብረ ኃይሉ ርምጃ እንደሚወስድ አስታወቀ

## - ለመጪው የገና በዓል በቂ የምርት አቅርቦት እንዲኖር ዝግጅት እየተደረገ ነው

ሰሚራ በርሀ

አዲስ አበባ፡- መጪውን የገና በዓል አስመልክቶ ያልተገባ የዋጋ ጭማሪ የሚያደርጉ ነጋዴዎች ላይ የቁጥጥር ግብረ ኃይሉ ርምጃ የሚወስድ መሆኑን የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ ገለጸ፡፡ ለመጪው የገና በዓል በቂ የምርት አቅርቦት እንዲኖር ዝግጅት እየተደረገ መሆኑ ተጠቁሟል፡፡

ከአዲስ ዘመን ጋር ቆይታ ያደረጉት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንግድ ቢሮ የግብይትና የገበያ ልማት ዘርፍ ምክትል ኃላፊ አቶ ፍሰሀ ጥበቡ፤ በበዓል ወቅት የሚፈጠረውን የአቅርቦት እጥረት ለመፍታት በምክትል ከንቲባ የሚመራ ግብረ ኃይል ተቋቁሟል፡፡ ግብረ ኃይሉ በቂ የሆነ ምርትን ለተጠቃሚው ከማቅረብ ባሻገር ሕገ-ወጥ የንግድ እንቅስቃሴንም የሚቆጣጠር ነው፡፡

መጪውን የገና በዓል አስመልክቶ በቂ ምርት በመኖሩ በምርቶች ላይ የሚደረጉ ያልተገቡ የዋጋ ጭማሪዎች አይኖሩም ያሉት ምክትል ኃላፊው፤ በሀገር አቀፍ ደረጃ በቂ የእህል፣ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት አለ፡፡ ይህ ሆኖ ሳለ ያልተገባ የዋጋ ጭማሪ የሚያደርጉ ነጋዴዎች ካሉ የተቋቋመው ግብረ ኃይል ርምጃ እንደሚወስድ ገልጸዋል፡፡

እንደ ኃላፊው ገለጻ፤ መጪው የገና በዓልን አስመልክቶ የሰብል ምርት፣ የአትክልትና ፍራፍሬ እንዲሁም የኢንዱስትሪ ምርቶችን በበቂ ሁኔታ ለማቅረብ ዝግጅት እየተደረገ ነው፡፡ ለግብይት ሥርዓት ምቹ የሆኑ አማራጭ የግብይት ስፍራዎች እየተዘጋጁ ነው፡፡ ማህበረሰቡ የሚፈልጋቸውን የሰብል፣ አትክልትና ፍራፍሬ ፣ የኢንዱስትሪ ውጤቶችና የእንስሳት ተዋጽኦ ውጤቶችን በባዛር ፣ በቅዳሜና እሁድ ገበያ እንዲሁም በመደበኛ የግብይት ቦታዎች ላይ የሚቀርብ ይሆናል፡፡

በከተማዋ በ11 ክፍለ ከተሞች ላይ በባዛር ገበያ፣ በገበያ ማዕከላት እና በግብርና የገበያ ማዕከላት ላይ በቂ የምርት አቅርቦት ለማድረስ ታቅዷል የሚሉት ኃላፊው፤ በምርቶች ላይ ያለውን የአቅርቦት ችግር ለመፍታት በየአካባቢው የተቋቋመው የእሁድ ገበያ የገና በዓል ከመድረሱ አስቀድሞ እስከ በዓሉ እለት በየቀኑ አገልግሎት እንደሚሰጡም ተገልጿል፡፡

እንደ ምክትል ኃላፊው ገለጻ፤ የቁም እንስሳት አቅርቦት ላይ በቂ ዝግጅት የተደረገ ሲሆን፤ የቁም እንስሳት ግብይት በሚደረግባቸው ማዕከላት በበቂ ሁኔታ ለማቅረብ ዝግጅት ተደርጓል፡፡ የአዲስ አበባ ንግድ ሥራዎች ድርጅት ማዕከል የሆኑ ቦታዎች ፣ በመደበኛነት አገልግሎት በሚሰጡ የግብይት ስፍራዎች ፣ የኅብረት ሥራ ማህበራት ፣ የገበያ ማዕከላት እንዲሁም የከተማ ግብርና ቦታዎች የሚያከናውኑት ሽያጮች ተጠናክረው ይቀጥላሉ፡፡

ግብረ ኃይሉ በበዓል ወቅት የሚኖረውን ከፍተኛ የግብይት ፍላጎት አስመልክቶ በገበያው ላይ ባልተገባ ሁኔታ የማህበረሰቡን ጤና የሚጎዱ ባዕድ ነገር የተቀላቀለባቸው ምርቶች ፣ የመጠመቀሚያ ጊዜያቸው ያለፈባቸው የኢንዱስትሪ ምርቶችን ይቆጣጠራል ሲሉ ኃላፊው ገልጸዋል፡፡ በዚህ ተግባር ላይ ሲሰማሩ የተገኙ ነጋዴዎችም ሕጉን ተከትሎ አፋጣኝ ርምጃ ይወስዳልም ብለዋል፡፡

ግብረ ኃይሉ የተውጣጣው ከአዲስ አበባ ከተማ ንግድ ቢሮ ፣ የአዲስ አበባ ህብረት ሥራ ኮሚሽን፣ ከአዲስ አበባ ንግድ ሥራዎች ድርጅት፤ ከከተማ ግብርና እና የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን ያካተተ መሆኑንም ጠቅሰዋል፡፡

ግብረ ኃይሉ ሦስት ዘርፎች ያሉት መሆኑን የሚናገሩት የቢሮው ኃላፊ፤ የአቅርቦት ዘርፍ፣ የሕገ-ወጥነትና የኢንስፔክሽን፣ ድጋፍና ክትትል የተባሉ ዘርፎችን የያዘ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

ኅብረተሰቡ ግብይት በሚያደርግበት ወቅት የሚመለከታቸውን ሕገ-ወጥ ተግባራት ቢሮው ባዘጋጀው ነጻ የጥቆማ የስልክ መስመር 8588 ላይ እና በየገበያ ማዕከላት በየወረዳው ጥቆማ ማድረግ እንደሚችል ጠቁመዋል፡፡

# ኢትዮጵያ የጋራ በሆኑ..

ከገጽ 1 የዞረ

ኢትዮጵያ ለጎረቤት ሀገራት ሰላም አስተዋጽኦ የምታደርገው በሰው ሀገር ውስጥ ሆና ነው፡፡ ይህም የመሳካት ዕድሉ የሚወሰነው በአብዛኛው በኢትዮጵያ ፍላጎት ብቻ ሳይሆን በዚህ ሀገር ፍላጎት ጭምር ነው ያሉት የፖለቲካ ተንታኙ፤ ለአብነት በደቡብ ሱዳን ሰላም እንዲመጣ ኢትዮጵያ የበኩሏን ድርሻ መወጣቷን ጠቅሰዋል፡፡ በደቡብ ሱዳን ለኢትዮጵያ ጥሩ ተደማጭነት ያለ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

በሌላም በኩል በሌሎችም የጎረቤት ሀገራት ሰላም ለማምጣት ብዙ ጥረት ተደርጓል ያሉት የፖለቲካ ተንታኙ፤ ለአብነት ሱዳን ወደ ጦርነት ከመግባቷ አስቀድሞና ከገባች በኋላም፤ ኢትዮጵያ ብዙ ጥረት አድርጋለች። ነገር ግን ሱዳን ላይ ሰላም እናመጣለን የሚሉ ብዙ ተዋናዮች በመግባታቸው ተጨማሪ ራስ ምታት ላለመሆን ለሌሎች ዕድሉን መስጠቷን ተናግረዋል፡፡

ኢትዮጵያ በማደራደርም የተሻለ ሰላም እንዲመጣና ግጭቶች እንዲቆሙ ለማድረግ ጥረት እንደምታደርግ የተናገሩት ዳርእስከዳር (ዶ/ር)፤ ለጎረቤት ሀገራት ብቻ ተብሎ አይሠራም፤ የራስ ሥራም ይሠራል ብለዋል፡፡ አያይዘውም ኢትዮጵያ በሰላም ጉዳይ ላይም ሆነ በሌሎች የጋራ በሚያደርጉ ጉዳዮች ላይ ከጎረቤት ሀገራት ጋር አብራ ለመሥራት ፈቃደኛ መሆኗን ጠቁመዋል፡፡

ዜና

# "ውጤታማና የላቀ የፍትሕና የዳኝነት አገልግሎትን ለመስጠት ሀገር አቀፍ የሪፎርም ሥራዎች እየተሠሩ ነው"

- ዶክተር ኤርሚያስ የማነብርሃን
የፍትሕ ሚኒስትር ዴኤታ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ ፡- ሕገ መንግሥታዊ መርህን መሰረት በማድረግ ነጻነትና ተጠያቂነት ሚዛናቸውን ጠብቀው እንዲተገበሩ የሚያስችሉና ውጤታማ የፍትሕና የዳኝነት አገልግሎትን ለመስጠት እንዲቻል ሀገር አቀፍ የሪፎርም ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑን የፍትሕ ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር ኤርሚያስ የማነብርሃን አስታወቁ፡፡

ዶክተር ኤርሚያስ የማነብርሃን በተለይም ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል እንደተናገሩት፤ ነጻነትና ተጠያቂነት የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች እንደመሆናቸው በፍትሕ ሥርዓቱ የዳኞች ነጻነት በሚገባ የሚጠበቅበትና ከዚሁ ጎን ለጎንም ዜጎችን የሚጎዱ ተግባራትን ለመከላከል ተጠያቂነትን ለማስፈን የሚያስችል የሪፎርም ሥራ በመተግበር ላይ ነው ብለዋል፡፡



የለውጡ መንግሥት እንዲመጣ ምክንያት የሆነው የሕዝብ ሮሮ እና ምሬት ለተገለጸበት ተቃውሞ ዋነኛ ምክንያት ከነበሩት ምክንያቶች ውስጥ ዋነኞቹ በፍርድ ቤት ነጻነትና ገለልተኛነት ላይ የሚደርሰው ያልተገባ ጣልቃ ገብነትና ጫና፣ የሰብአዊ መብት ጥሰት፣ የፍትሕ መጓደል እና አድሏዊነት እንደነበሩ አመልክተዋል።

የሪፎርሙ ሥራ መነሻም እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍ ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በመጀመሪያ የፓርላማ ንግግራቸው የሕግ የበላይነትን ለማስፈን፣ የዳኝነት ነጻነትን ለማረጋገጥና የሕዝብን የፍትሕ ፍላጎት ለማረጋገጥ እንደሚሠራ መግለጻቸው እንደነበር ጠቁመዋል።

እንደ ዶክተር ኤርሚያስ የማነብርሃን ገለጻ፤ ከለውጡ በፊት የዳኞች ምልመላ፣ አሿሿምና ዝውውር በፖለቲካ የተቃኘ ስለነበር ዘርፉ በበርካታ ውስብስብ ችግሮች የተበተበተ በመሆኑ በፍትሕ ሥርዓቱ ላይ የዜጎች ቅሬታ ከፍተኛ ነበር፡፡ ይሁንና ከለውጡ ዘመን ወዲህ የፍትሕ ሥርዓቱን ውጤታማና የላቀ ለማድረግ በሕገ መንግሥታዊ መርህ መሠረት የዳኞች ነጻነት እና ተጠያቂነት ሚዛኑን የጠበቀ እንዲሆን የሚያስችል የሪፎርም ሥራ በመተግበር ውጤት ታይቷል፡፡

የሕግ ተርጓሚ ተቋማት ላይ እየተሠራ ያለው የሦስት ዓመቱ የሪፎርም ሥራ የዳኝነት ነጻነትን መሰረት በማድረግ በፍርድ ቤቶች በራሳቸው በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትና በየክልሉ በሚገኙ ምክር ቤቶች ክትትልና ድጋፍ በፌዴራል ፣ በክልሎችና በከተማ አስተዳደሮች እየተተገበረ እንደሚገኝ አመልክተዋል። ሦስት ዓመቱ የዳኝነትና የፍትሕ ዘርፍ ሪፎርም ያካተታቸው አስር የለውጥ አምዶችን ለማሳካት አንድ ዓመት ከስድስት ወራት የማጠናቀቂያ ጊዜ እንደሚቀረውም ጠቁመዋል።

ሮም ባንድ ቀን ባትገነባም በየቀኑ እየተገነባች እና እየተሠራች ታላቅ ከተማ እንደሆነች ሁሉ በቀሪው የሪፎርም ማስተግበሪያ ጊዜ ውስጥ ቀሪ ሥራዎችን በማጠናቀቅ፤ የታዩ ክፍተቶችን በመሙላት ለዳኝነትና የፍትሕ ሥራዎች ሮሮና ቅሬታዎች ምላሽ በመስጠት የሕዝብ አመኔታን በላቀ መልኩ የማሳደግ ሥራዎች

# "በባሕር በር ጉዳይ መላው የኢትዮጵያ...

ያመለከቱት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ በወቅቱም ለእሳቸው ያላቸውን ከፍተኛ ፍቅር እና አክብሮት ገልጸዋል። ኢትዮጵያ የምታካሂደው የኢኮኖሚ ሪፎርም እንዲሳካ ከፍተኛ ድጋፍ ማድረጋቸውን በመጥቀስም፤ ለፕሬዚዳንቱ ከፍያለ ምስጋና አቅርበዋል። ወደፊትም ድጋፋቸው እንዳይለያቸው ጥሪ አቅርበዋል።

"በጣም በርካታ የሁለትዮሽ እና ባለብዙ ዘርፍ ጉዳዮች ዙሪያ ተነጋግረናል። በዚህም በአፍሪካዊ እና በአውሮፓዊ ጉዳዮች ዙሪያ ተደጋግፈን ለመሥራት ተግባብተናል ። ከፈረንሳይ ጋር የነበረን የመቶ ሃያ ሰባት ዓመታት ዲፕሎማቲክ ግንኙነት የበለጠ ተጠናክሮ ለትውልድ እንዲሻገር በእኔም ሆነ በእሳቸው በኩል አበክረን እንድምንሠራ ቃል ተግባብተናል"ብለዋል። ለነበራቸው ጊዜ ፣ ድጋፍ እና ለጉብኝታቸውም በራሳቸው እና በኢትዮጵያ መንግሥት ስም ከፍተኛ ምስጋና አቅርበዋል።

የፈረንሳዩ ፕሬዚዳንት ኢማኑኤል ማክሮን በበኩላቸው፤ የኢትዮጵያ የባሕር በር ጥያቄ ትክክለኛ ነው፤ ጥያቄው ምላሽ እንዲያገኝ ፈረንሳይ ባላት አቅም ማድረግ የምትችለውን እንደምታደርግ አስታውቀዋል።

ጥያቄው በንግግር እና በውይይት፤ ዓለም አቀፍ ሕጎችን እና ጎረቤት ሀገራትን ባከበረ፤ኢትዮጵያን እና ክልሉን በሚጠቅም መልኩ ሊከናወን እንደሚገባ ያመለከቱት ፕሬዚዳንቱ፤ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ በቱርክ ከሶማሊያው ፕሬዚዳንት ጋር የሰላም ንግግር ማድረጋቸው የሚደገፍ እንደሆነም ጠቁመዋል።

ፈረንሳውያን ለባሕል እና ለቅርስ ትልቅ ቦታ እንደሚሰጡ ያመለከቱት ፕሬዚዳንት ኢማኑኤል ማክሮን ፤ በቅርቡ የእሳት አደጋ የደረሰበትን የኖተራንዳም ቤተክርስቲያናችን እንደ አዲስ ታድሶ ለሕዝብ ክፍት መደረጉን፤ በዚህም ፈረንሳውያን በጣም እንደሚኮሩ አስታውቀዋል።

"በቤተመንግሥት እድሳቱ ትላልቅ እና አዋቂ ብለን የምናስባቸው ትውልደ ፈረንሳይ እና ፈረንሳውያን አርክቴክቶች ፣ የሙዚየም እድሳት ባለሙያዎች እና የተለያዩ እውቀት ባለቤቶች ልከናል፤ የአቅማቸውን ማበርከት ችለዋል፤ በዚህም እንኮራለን፤ ሥራው ለእኛም በጣም ኩራት ነው" ብለዋል።

በሰሜን ኢትዮጵያ ሰላም ማስፈን ይቻል ዘንድ የፕሪቶሪያ ስምምነት ትልቅ እርምጃ መሆኑን፤ፈረንሳይ የስምምነቱን ተግባራዊነት እንደምትደግፍ አስታውቀዋል። የእርሻ ሥራን ማበረታታት፣ የተጎዱ ሆስፒታሎችን መልሶ መገንባት፣ ከዛም በተጨማሪ የሽግግር ፍትሕ ተግባራዊ የሚሆንበትን እና የሕግ የበላይነት የሚከበርበትን ሁኔታ ማየት እንፈልጋለን ፤ለዚህም እንደቀደመው የሚያስፈልገውን ድጋፍ መስጠታቸውን እንደሚቀጥሉ አስታውቀዋል።

"ኢትዮጵያ ቀደምት ከሚባሉ ሀገራት አንዷናት። እዚህ በመገኘቴ በጣም ደስተኛ ነኝ ። ይቺ ሀገር በአፍሪካ ታላቅ እና ተስፋ ያላት ሀገር ነች ብዬ ልገልጽ እወዳለሁ። እዚህ ያለነው እንደ ጓደኛ እና ወዳጅ ጭምር ነው። ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር በእርሶ እንደምተማመንብዎት ልገልጽልዎት እወዳለሁ፤ ፈረንሳይም በኢትዮጵያ ትተማመናለች" ብለዋል።

እኛን የሚያገናኘን የወጣቶቻችን የወደፊት ትክክለኛ እጣ ፈንታ ነው። ለዚህም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ኃላፊነታቸውን መወጣት በመቻላቸው ላመሰግን እወዳለሁ። ለወደፊት ቀጣናው ሰላማዊ እና የበለጸገ እንዲሆን ኢትዮጵያ የሚኖራት አስተዋጽኦ ከፍተኛ እንደሚሆን ያላቸውን ምኞት ገልጸዋል።

ፕሬዚዳንት ኢማኑኤል ከጉብኝታቸው በኋላ በኤክስ ገጻቸው በአማርኛ ቋንቋ ባስተላለፉት መልዕክት፤ ኢትዮጵያ ለሰው ልጅ መገኛነት የመጀመሪያ አሻራ ያላት ሀገር ናት። በኢትዮ-ፈረንሳይ መካከል ያለው ግንኙነት በታሪክ ሂደትና በትላልቅ የጋራ ፕሮጀክቶች ላይ የተመሠረተ ነው ብለዋል።

እ.ኤ.አ በ2019 መሠረታዊ የሆኑ የባህልና የቅርስ ጥበቃን ከሳይንሳዊ ፕሮግራም ጋራ አያይዘን ለመሥራት ወስነን ተነስተናል፤ በላሊበላም የሠራነው በዓለም ላይ ልዩ የሆነ የቅርስ ጥበቃ ፕሮጀክት በሚቀጥሉት ወራት ውስጥ ፍጻሜውን እንደሚያገኝ አመልክተዋል።

በአንድ ወቅትም የብሔራዊ ቤተ መንግሥት እድሳት ፕሮጀክትንም ሠርተን ዛሬ የሚያኮራ እውነታ ሆኖ እየታየ ነው። ወደፊትም የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ማሻሻያ ማዘመንን ለመደገፍ እና በትግራይ የሰላምና የመረጋጋት መሠረት የሆነውን የፕሪቶሪያ ስምምነትን ተግባራዊ ለማድረግ ትብብር እናደርጋለን ብለዋል።

በመልዕክታቸው የተከበሩ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ የወደፊቷ የኢትዮጵያ ተስፋ የብልፅግናና የሰላም እንደሚሆን ፈረንሳይ እምነቷ ነው ብለዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በበኩላቸው በማህበራዊ ገጻቸው ባስተላለፉት መልእክት ከፕሬዚዳንት ኢማኑኤል ማክሮን ጋር በብሔራዊ ቤተመንግሥት በነበረን የሁለትዮሽ ውይይት ሰፋ ያለ መጠነ ርዕይ ባላቸው የሁለትዮሽ እና ባለብዙ ወገን ጉዳዮች ላይ ውይይት አድርገናል።

ክቡር ፕሬዚዳንት እና የፈረንሳይ መንግሥት በብሔራዊ ቤተመንግሥት በመካሄድ ላይ ባለው የላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት እድሳት ሥራዎች ላይ ላደረጉት አስተዋፅኦ ምስጋናዬን አቅርቤያለሁ።

በውይይታችን በተለያዩ ዘርፎች የሚኖሩ ትብብሮችን የፈተሸን ሲሆን የፈረንሳይን ኢንቨስትመንት መጨመርን አስመልክቶ ብሎም በትምህርት እና ባሕል ዘርፎች ያለንን ግንኙነት በማጠናከር ጉዳዮች ላይ



ተነጋግረናል። ታሪካዊ ትስስራችንን ይበልጥ የመገንባት አስፈላጊነትንም በውይይታችን አፅንኦት ሰጥቼ አንስቻለሁ ብለዋል ።

የጠቅላይ ሚኒስትር ቢሮ በበኩሉ የፕሬዚዳንቱን ጉብኝት አስመልክቶ በማህበራዊ ገጹ ላይ ባስተላለፈው መልእክት፤ ባለፉት ስድስት ዓመታት ውስጥ ለሁለተኛ ጊዜ ወደ ኢትዮጵያ ለጉብኝት የመጡትን የፈረንሳይ ፕሬዚዳንት ኢማኑኤል ማክሮንን ተቀብለዋል። ፕሬዚዳንቱ በ2011 ዓመተ ምህረት በነበራቸው ጉብኝት ለላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት የእድሳት ሥራ ድጋፍ እንደሚሰጡ አሳውቀው ነበር።

ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር በቅርቡ በታደሰው ብሔራዊ ቤተመንግሥት ክቡር ፕሬዚዳንቱን የተቀበሉ ሲሆን፤ ቤተመንግሥቱንም ተዘዋውረው ጎብኝተዋል። በሁለትዮሽ ውይይታቸው ወቅት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ፈረንሳይ ለብዙ ዘመናት ተዘንግቶ ለቆየው የብሔራዊ ቤተመንግሥት እድሳት ላደረገችው የእድሳት ድጋፍ አመስግነዋል።

ፕሬዚዳንት ኢማኑኤል በበኩላቸው፤ አስደማሚውን የቤተ መንግሥት እድሳት አድንቀው፤ በዓድዋ መታሰቢያ ግንባታ እንደታየው የኢትዮጵያን ታሪክ እና ባሕል ለማክበር የተደረገውን ጥረት ክብር ሰጥተዋል።

መሪዎቹ ሰፊ መጠነ ርዕይ ባላቸው የሁለትዮሽ እና ባለብዙ ወገን ጉዳዮች ላይ ውይይት ያደረጉ ሲሆን፤ በኢንቨስትመንት፣ ባሕል እና ትምህርት ትብብር ለማጠናከር ተስማምተዋል።

የኢትዮጵያን የባሕር በር ጥያቄ በተመለከተም ረጅም ዘመን ለቆየው መሻት ዘላቂ መፍትሔ ለማስገኘት ሁለቱ ወገኖች በጋራ ለመሥራት ያላቸውን ቁርጠኝነት ገልጸዋል።


ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ እና ፕሬዚዳንት ኢማኑኤል ማክሮን የነበራቸውን ውሎ የጋራ ፍላጎታቸውን የትብብር ቁልፍ ጉዳዮች በተመለከተ የጋራ መግለጫ በመስጠት አጠናቀዋል።

ፕሬዚዳንቱበአዲስአበባቆይታቸው ለጥቁርሕዝቦች ነፃነት ትግል መስዋዕትነት ለከፈሉ ጀግኞች መታሰቢያ ሀውልት ስር የአበባ ጉንጉን አስቀምጠዋል።የዓድዋ ድል መታሰቢያንም ጎብኝተዋል።አዲስ አበባ ባሳየችው ፈጣን ለውጥ አድናቆታቸውን ገልጸዋል።

# የፕሬዚዳንት ኢማኑኤል ማክሮን የአዲስ አበባ ጉብኝት በፎቶ



ፎቶ፡- በጠቀባዩ ሚኒስትር ቢሮ















# ርዕሰ አንቀፅ

## የፈረንሳይ መንግሥት ለቅርሶች እድሳት የሚያደርገው ድጋፍ ለታሪክ ያለውን ከበሬታ በተጨባጭ ያሳየ ነው!

ሀገራችን የተለያዩ ሃይማኖቶች እና ብሔር ፣ ብሔረሰቦች መኖሪያ ከመሆኗ ጋር በተያያዘ የብዙ ማኅበራዊ እና ሃይማኖታዊ እሴቶች እና ቅርሶች ባለቤት ሆናለች። ካሳለፈችው የረጅም ዘመን ሀገረ መንግሥት ታሪክ አንጻርም በየዘመኑ የነበሩ ነገሥታት ጥለዋቸው የሄዷቸው ዐሻራዎች የየዘመኑ አስተሳሰብ እና የሥነ ጥበብ መገለጫ በመሆን ዘመናትን አሻግረው ማየት ያስቻሉ መስታወቶቻችን ናቸው።

እንደ ሀገር እኛ ኢትዮጵያውያን ዓለምን በብዙ መልኩ መገረም እና መደነቅ ውስጥ የሚከቱ፣ የብዙዎችን አፍ በእጅ ያስጫኑ ፣ ዛሬም ድረስ ለዓለም ድንቅ የሆኑ ቅርሶች ባለቤቶች ነን። የአክሱም ሀውልቶች ፣ የላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት ፣ በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች የሚገኙ ቤተመንግሥቶች ፣ ገዳማት እና አድባራት ዘመን ተሻግረው ዛሬ ላይ ያሉ የተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦች ባህል እና ባህላዊ እሴቶች ከብዙ በጥቂቱ ተጠቃሾች ናቸው።

አብዛኞቹም በዓለም አቀፍ ደረጃ በዩኔስኮ እውቅና አግኝተው ዓለም አቀፍ ጥበቃ የሚደረግላቸው ቢሆኑም፤ ቀደም ባሉት ጊዜያት እነዚህን ሀብቶች ጠብቆ እና አልምቶ ሀገራዊ ተጠቃሚነትን ተጨባጭ ለማድረግ የተደረጉ ጥረቶች እዚህ ግባ የሚባሉ አይደሉም። ከታሪክ እና ከማንነት ማድመቂያነት ባለፈ ዘመኑን በሚመጥን መንገድ አስበን እና አቅደን ተገቢውን ጥበቃ አላደረግንላቸውም።

ከዚህም የተነሳ አብዛኞቹ ቅርሶች ከእድሜ እና ከተለያዩ ሰው ሰራሽ ችግሮች ጋር በተያያዘ ለተለያዩ አደጋዎች ተጋልጠው ቆይተዋል። አንዳንዶቹም በሚታይ አደጋ ውስጥ ወድቀው ለህልውናቸው የዓለም አቀፉን ኅብረተሰብ ድጋፍ ለመጠየቅ የተገደድንበት ሁኔታ መፈጠሩ የአደባባይ ምስጢር ነው።

እንደ ሀገር የመጣንበት መንገድ ለታሪክ እና ታሪክ ለሚፈጥሯቸው ትርክቶች በብዙ መልኩ ቅርብ ብንሆንም፤ ለታሪካዊ ትርክቶቻችን መሰረት ለሆኑት ቅርሶቻችን ተገቢውን ትኩረት መስጠት የሚያስችል የአስተሳሰብ መሠረት አልነበረንም። በዚህም የብሔራዊ ክብራችን መሠረት የሆኑ ቅርሶቻችን ለከፋ አደጋ ተጋልጠው እና ተመልካች አጥተው የብዙዎችን ልብ አድምተው ኖረዋል።

ይህን ሀገራዊ እውነታ ለመቀየር ባለፉት አምስት ዓመታት በመንግሥት በኩል ሰፊ ሥራዎች ተሠርተዋል። ቅርሶቹን አውቆ በመጠበቅ እና በማልማት ላይ የተመሰረተ አዲስ አስተሳሰብ በመፍጠር እና በመገንባት ቅርሶቹ በሀገር ኢኮኖሚ ውስጥ የሚኖራቸውን ጠቀሜታ በተጨባጭ እንዲያበረክቱ ብዙ ርቀት መጓዝ ተችሏል። በተለይም በቅርሶች እድሳት ዙሪያ እየተከናወኑ ያሉ ተግባራት በሀገሪቱ በዘርፉ አዲስ እሳቤ ስለመምጣቱ ተጨባጭ ማሳያ ሆኗል።

በመንግሥት በራሱ አቅም ሊታደሱ የሚችሉትን ቅርሶች በማደስ፤ ከቅርስነት ባለፈ የተሻለ ኢኮኖሚ ማመንጨት የሚችሉበትን አስቻይ ሁኔታ ለመፍጠር እየሠራ ነው። ለዚህም አሁን ላይ በእድሳት ላይ የሚገኙ የጎንደር እና የአባ ጅፋር ቤተመንግሥት ፣የሶፉመር ዋሻን እንደ ማሳያ መጥቀስ ይቻላል።

ከመንግሥት አቅም በላይ የሆኑትን ዓለም አቀፍ የትብብር ድጋፎችን በማፈላለግ የእድሳት ሥራቸው እንዲከናወን እያደረገ ነው። ለዚህም በፈረንሳይ መንግሥት የገንዘብ እና የቴክኒክ ድጋፍ እየተከናወኑ የላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት እና የኢዮቤልዩ ቤተመንግሥት እድሳት ተጠቃሽ ናቸው። ድጋፉ በሀገራቱ መካከል አዲስ የትብብር ምዕራፍ መከፈት ያስቻሉም ናቸው።

የፈረንሳይ መንግሥት ፣ በፕሬዚዳንት ኢማኑኤል ማክሮን በኩል፤ ቅርሶቹን ለማደስ እና ለማልማት እየተደረገ ያለው ድጋፍ የፈረንሳይ ሕዝብ ለቅርስ በተለይ ደግሞ ለኢትዮጵያውን ትናንቶች ያለውን ከፍ ያለ ከበሬታ በተጨባጭ ያሳየ ነው። በመላው ኢትዮጵያውያን እውቅና የተቸረው አዲስ የትብብር ምዕራፍ ጅማሬም ነው!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ
- አልማዝ አያሌው

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የሀገራቱ ስምምነት- በጋራ የመበልፀግ እሳቤ እውን እንዲሆን

አስናቀ ፀጋዬ

ኢትዮጵያ በቀደመ ታሪኳ በቀይ ባሕር ላይ በምሥራቅ አፍሪካ ግዙፍ የፖለቲካና የንግድ ተፅዕኖ የነበራት ሀገር ነች። በቀደሙት ዘመናት የሥልጣኔ ቁንጮና ስመ ገናና ሀገር ከምሥራቅ አፍሪካ ተሻግራ ከመካከለኛው ምሥራቅ፣ ከአውሮፓና ከእስያ ሀገራት ጋር ጠንካራ የንግድና የዲፕሎማሲ ግንኙነትም ስታደርግ ቆይታለች። ሀገሪቱ በቀይ ባሕር ዙሪያ ሁለንተናዊ ግንኙነት ስታደርግ የቆየችው በጊዜው የነበሯትን የባሕር በሮቿን ተጠቅማ ነበር።

የኢትዮጵያ ግዛት የነበረችው ኤርትራ በሕዝበ ውሳኔ ከተገነጠለች በኋላም የጎረቤት ሀገራት አማራጭ ወደቦችን በመጠቀም ከተቀረው ዓለም ጋር ያላትን የንግድ ግንኙነት ታስቀጥል እንጂ በቀይ ባሕር ላይ የነበራት የደኅንነትና የፖለቲካ ተፅዕኖ በእጅጉ አሽቆልቁሎ ነበር። ይህ አካሄድ የሀገሪቱን ሁለንተናዊ እድገት በሚፈለገው መጠን እንዳይፋጠን ከማድረግ ባለፈ በንግዱም ቢሆን ለከፍተኛ የወደብ ኪራይ ወጪ የዳረገ ነው።

ይህ ዘርፈ ብዙ ምክንያት ኢትዮጵያ የማይዋዥቅና አስተማማኝ የሆነ የንግድ እንቅስቃሴ የምታደርግበትን የንግድ ወደብ ጨምሮ ፖለቲካዊና ፍላጎቶቿን ጭምር የምታስተናግድበት ነፃ፣ ከጣልቃ ገብነት የተገደበ የባሕር በር እንደሚያስፈልጋት የሚጠቁም ነው።

ከኢኮኖሚና ንግድ አንፃር ጉዳዩን ከቃኘነው ኢትዮጵያ ከቀሪው ዓለም ጋር ያላትን የንግድ ትስስር ለማቀላጠፍና የገቢና የወጪ ንግድን ለማሳለጥ የጅቡቲን ወደብ በመጠቀም ረጅም ጊዜ አስቆጥራለች። አሁንም ቢሆን ‹‹የኢትዮጵያን ወጪና ገቢ ምርት በማሳለጥ ረገድ የጅቡቲ ወደብ ዋነኛ የልብ ትርታ ነው›› ማለት ይቻላል። ይሁን እንጂ በዋጋ መናርና በተለያዩ ምክንያቶች በየጊዜው የሚጨምረው የኪራይ ዋጋ የኢትዮጵያን ዘላቂ ልማት የሚያረጋግጥ አይደለም። ወደቡ ከንግድ ፍላጎቶች ባሻገር የኢትዮጵያን በቀይ ባሕር ላይ ያላትን ተፅዕኖ ለማሳደግ ፋይዳ ያለው ባለመሆኑም ሁለንተናዊ ጥቅምን ከማሳካት አንፃር ሚናው እዚህ ግባ የሚባል አይደለም።

በንግዱም ቢሆን አሁን ባለው ሁኔታ ኢትዮጵያ የጅቡቲን ወደብ ብቻ በመጠቀም ኢኮኖሚዋን ማሳደግ አትችልም። በቀይ ባሕር ላይ ያላትን ፖለቲካዊ ተፅዕኖ ለማሳደግም የኪራይ ወደብ ብቻ ተጠቃሚ መሆን በቂ አይደለም። በዚህ ምክንያት ከወደብ ባሻገር ቀደም ሲል በቀጣናው የነበራትን የቀይ ባሕር ተፅዕኖ የሚመልስ የባሕር በር ያስፈልጋታል።

እንደሚታወቀው የኢትዮጵያ መንግሥት ከጅቡቲ ወደብ ባለፈ የአሰብና በርበራ ወደቦችን በጋራ አልምቶ ለመጠቀም በተለያዩ ጊዜያት ጥያቄ ሲያቀርብ ቆይቷል። ለንግድ እንቅስቃሴ ከሚደረገው የወደብ ኪራይ ስምምነት የዘለለ የሀገሪቱን የቀይ ባሕር ተፅዕኖ ሁለንተናዊ በሆነ መልኩ የሚያጎላ ጥያቄ የለውጡ መንግሥት በአጀንዳነት እያቀነቀነ ነው። ይህ ጥያቄ ኢትዮጵያ የባሕር በር እንደሚያስፈልጋት በጉልህ የሚያሰምር ነው።

መንግሥት ኢትዮጵያ የባሕር በር የማግኘት ተፈጥሯዊ፣ ሕጋዊና ታሪካዊ መብት እንዳላት ከማንሳት በዘለለም ለተግባራዊነቱ መሬት የወረደ እርምጃዎችን ወስዷል። ከሶማሌ ላንድ ጋር ለወታደራዊና ለንግድ አገልግሎት የሚውል የባሕር በር ማግኘት የሚያስችል የመግባቢያ ስምምነት መፈራረሙ የቅርብ ጊዜ ትውስታ ነው። ይሁን እንጂ ይህ እርምጃ በብዙዎች ዘንድ አቧራ ያስነሳ ነበር።

በተለይ ስምምነቱ ያልተዋጠላት ሶማሊያ ‹‹ሉዓላዊነቴ ተደፍሯል›› በማለት ክስ በማቅረብ ነገሩን በአግባቡ ካለመረዳት እና በሌሎች ሀገራት ጫና ውስጥ እንድትቆይና በቀጣናው ውጥረት እንዲፈጠር ምክንያት ሆና ቆይታለች።

ጉዳዩ ከውጪ ብቻ ሳይሆን ከሀገር ውስጥም ጭምር ትኩረትን የሳበ ቢሆንም ኢትዮጵያ የባሕር በር የማግኘት ፍላጎቷን ለማሳካት የሚፈለገውን ሕጋዊ እርምጃዎች እንደምትወስድ ያረጋገጠ ነበር። ይህ ታሪካዊ ውሳኔ በአንዳንድ የኢትዮጵያውያን ዘንድ አሉታዊ ጥርጣሬም የፈጠረ ነበር። ሶማሊያም በግብፅ በሚደርስባት ተፅዕኖ በመነሳትና በአጉል ጥርጣሬ ጥያቄውና አካሄዱ ሉዓላዊነቴን የሚዳፈር ነው በማለት ተደጋጋሚ ክስና ዛቻዎችን ስትሰነዝር ተደምጣለች።

እውነታው ግን ኢትዮጵያ እያደገ የመጣውን የኢኮኖሚ ደረጃ የሚመጥን የወደብ አገልግሎት እንዲሁም ከኢኮኖሚያዊ ፍላጎቶች የተሻገረ ፖለቲካዊ ተፅዕኖዋን በቀይ ባሕር ላይ የሚያጎላ የባሕር በር እንደሚያስፈልጋት በማመኗ በሠላማዊ መንገድ ጥያቄ ማቅረቧ ነው።

ከላይ ባነሳነው መሠረታዊ ምክንያት በተለይ የውጪ ኃይሎች በሚፈጥሩት ጣልቃ ገብነት እና ጫና በሁለቱ ሀገራት መካከል የተፈጠረውን ውጥረት ለማርገብ ሙከራዎች ተደርገዋል። በዚህም አለመግባባቱን በሠላማዊ መንገድ ለመፍታት ኢትዮጵያና ሶማሊያ በቱርክ አንካራ ለድርድር መቀመጣቸው ይታወሳል።

በሦስት ዙር በተካሄደው በዚህ ድርድር የኢትዮጵያን የባሕር በር ጥያቄና ፍላጎት እንዲሁም የሶማሊያን ሉዓላዊነት ባከበረ መልኩ እንዲፈፀም ስምምነት ላይ ተደርሷል። ስምምነቱ ለኢትዮጵያን ታላቅ የዲፕሎማሲ ድል ተደርጎ የሚወሰድ ነው። በአንካራው ስምምነት ኢትዮጵያም ሆነ ሶማሊያ በትብብር ለጋራ ብልፅግና ወደፊት መሥራት እንዳለባቸው ተገልጿል። በዚህም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ኢትዮጵያ ላነሳችው የባሕር በር ጥያቄ እውቅና አግኝታለች።

የአንካራው ድርድር በሉዓላዊ ሶማሊያ መንግሥት ስር ኢትዮጵያ አስተማማኝ፣ ደኅንነቱ የተጠበቀና ዘላቂ የባሕር በር እንድታገኝ የሚያስችል፤ ለሁለቱም ሀገራት ጠቃሚ የሆኑ የኪራይ፣ የኮንትራትና ተመሳሳይ የንግድ አሠራር መንገዶችን በጋራ በመሆን ለማጠናቀቅ መስማማታቸው የኢትዮጵያን የባሕር በር ጥያቄ እንደሚመልስ ይታመናል።

ከሁለቱ ሀገራት በሚውጣጡ የቴክኒክ ኮሚቴ አባላት በሚደረገው ቀጣይ ስምምነት ኢትዮጵያ አስተማማኝ የባሕር መተላለፊያ ለማግኘት የሚያስችል የተሟላ ስምምነት ላይ ከደረሱ ለሀገራችን ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ይኖረዋል። በተለይ በዚህ የወቅቱ የሀገራችን አንገብጋቢ ጥያቄ ዙሪያ ሶማሊያ እውቅና መስጠቷ በጋራ ለመልማት ያላትን ፍላጎት የሚያሳይና ለድርድሩ ተፈፃሚነት በር ከፋች ነው። ይህም በየካቲት ወር መጨረሻ ሁለቱ ሀገራት በቴክኒካዊ ጉዳዮች ላይ ለሚያደርጉት ውይይት በተለይ ለኢትዮጵያ ትልቅ ግብዓት ሆኖ ያገለግላል።

ከዚህ ቀደም አትዮጵያ ሕዝቦቿን በኢኮኖሚና ለመለወጥና በቀይ ባሕር ዙሪያ ያላትን ሁለንተናዊ ተፅዕኖ ለማሳደግ የጋራ ተጠቃሚነትን መርሕ መሠረት ባደረገ መልኩ ሶማሊያን ጨምሮ የሌሎች የምሥራቅ አፍሪካ ሀገራት ያቀረበችው ጥያቄ በብዙዎች ዘንድ ሲጥላላና ሲናናቅ ቆይቷል፤ ይህ ፍፁም ስህተት እንደነበር የቅርብ ጊዜዎቹ አለመግባባቶች ያመለክታሉ። ምክንያቱም አሁን ላይ የዚህች ታላቅ ሀገር የባሕር በር ጥያቄ ከማይቀለበስበት ደረጃ ላይ ደርሷል፤ በዓለም አቀፍ ደረጃም ምላሽ እንደሚያሻው እየታመነበትና ፈር እየያዘ መጥቷል።

ቀጣዩ የቤት ሥራ ቀጥተኛ የባሕር በር ተጠቃሚ የሚያደርገንን ጥያቄ በሠላማዊ መንገድ አጠናክሮ ማስቀጠል ነው። በተለይ ከሶማሊያ ጋር የተደረገው ስምምነት ተከትሎ የሚደረጉ ዝርዝር የአፈፃፀም ድርድሮችን የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም ባስጠበቀ መንገድ እንዲፈፀም መሥራት ይገባል። ስምምነቱ ሳይሸራረፍ ገቢራዊ ማድረግና ለተግባራዊነቱ ሌት ተቀን መሥራት ያስፈልጋል።

መላው ኢትዮጵያውያንም ለልጆቻቸው፣ ለልጅ ልጆቻቸውና ለመጪው ትውልድ የሚጠቅምና የቀድሞውን ኃያልነታችንን የሚመልስ የባሕር በር የማግኘት ሠላማዊ ጥያቄ እውን እንዲሆን በፍላጎት መደገፍ ይጠበቅባቸዋል። ጊዜው ከተናጠል ይልቅ በትብብር መሥራትን የሚጠይቅ ከመሆኑ አንፃር ሁሉም የቀጣናው ሀገራትም ቢሆኑ ይህንን ከግምት ውስጥ በማስገባት በጋራ አልምተው በጋራ የሚለወጡበትን አካሄድ ይከተላሉ ተብሎ ይጠበቃል!!

ፖለቲካ እና ወቅታዊ
ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

# “ነፍሰ-ገዳይነት” በኢትዮጵያ የወንጀል ሕግ

**ይግረማቸው ከፈለኝ ወግደረስ (LLB, LLM)**
**ጠበቃ፣ የሕግ አማካሪ እና በወንጀል ፍትሕ አስተዳደር አሠልጣኝ**
**0910037554/yigremachewk@gmail.com**

“አትግደል” የሚለው በሁሉም ሃይማኖቶች ውስጥ ያለው መንፈሳዊ ሕግ በጦርነት ሕግ እና በተለዩ-ጉዳዮች የወንጀል ቅጣት እንዲሆን ተፈቅዶ ካልሆነ በስተቀር በምድር ሕግጋትም የፀና ሕግ ነው። ሰው መግደል በየትኛውም ዘመናዊ የሕግ ሥርዓት ከፍተኛ ቅጣት የሚያስቀጣ በሰው የሕይወት መብት ላይ የሚፈፀም ደረቅ ወንጀል ነው።

የሕይወት መብት የመጀመሪያ ትውልድ ከሆኑት ሰብዓዊ መብቶች ውስጥ ቀድሞ የሚጠቀስ እጅግ መሠረታዊ መብት ነው። የሌሎች መብቶች ሁሉ ማደሪያውም ይኸው መብት ነው ለማለት ይቻላል። ለዚህም ይመስላል የ1960 የፍትሐብሔር ሕጋችን አንቀፅ 1 ስር “ሰው ከተወለደበት ቀን አንስቶ እስከ ሞተበት ቀን ድረስ የሕግ መብት አለው” በማለት የሚጀምረው።

የሕይወት መብት ሰብዓዊ ብቻ ሳይሆን ሕገ-መንግሥታዊ መብትም ነው። የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግሥት አንቀፅ 15 ስር “ማንኛውም ሰው በሕይወት የመኖር መብት አለው። ማንኛውም ሰው በሕግ በተደነገገ ከባድ የወንጀል ቅጣት ካልሆነ በስተቀር ሕይወቱን አያጣም” በማለት የሕይወት መብትን ደንግጎ ይገኛል።

የሕይወት መብትን አስመልክቶ ሀገራት የሞት ቅጣትን በሕጋቸው ውስጥ ማስቀመጣቸው ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ወቅት በሕይወት የመኖር መብት ከሚገደቡት መብቶች ውስጥ ሊመደብ ይገባል ወይስ አይገባም? በሕይወት የመኖር መብት ከሌሎች በተለይም ከ4ኛ ትውልድ ሰብዓዊ መብቶች ጋር ያለው ግንኙነት እንዴት ይታያል የሚሉ እና ሌሎች ጉዳዮች በሕግ ጁሪስፕሩደንስ (በሕግ ሳይንስ) ውስጥ አሁንም የመወያያ አጀንዳዎች ናቸው። የዚህ አጭር ጽሑፍ ዓላማ ግን በሰው ሕይወት ላይ የሚፈፀም ወንጀል በ1996 ዓ.ም የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የወንጀል ሕግ አንፃር እንዴት ይታያል የሚል ነው።

**ነፍሰ ገዳይነት ምንድነው?**

የ1996 ዓ.ም የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የወንጀል ሕግ የሚሰርቅ ሰው ሌባ ነው፤ ውንብድና የሚፈፅም ሰው ወንበዴ ነው፤ የአታላይነት ወንጀል የሚፈፅም ሰው አታላይ ነው...ወዘተ በማለት ስያሜ አይሰጥም። ነገር ግን በአንድ ጉዳይ ላይ ወንጀሉን ለሚፈፅመው ሰው ስያሜ ሲሰጥ እንመለከታለን። የወንጀል ሕጉ አንቀፅ 538 (1):- “ማንም ሰው አስቦ ወይም በቸልተኝነት በማናቸውም አይነት መሣሪያ ወይም ዘዴ ሌላውን ሰው የገደለ እንደሆነ ነፍሰ-ገዳይ ነው” በማለት በዚህ ጉዳይ ላይ ብቻ ድርጊቱን ለሚፈፅሙ ሰዎች ስያሜ ሰጥቷል። ታዲያ የዚህ ምክንያቱ ምንድነው ያልን እንደሆነ አንድም በሀገራችን “ነፍሰ-ገዳይነት” የሚለው ስያሜ አሉታዊ ኃይል እንዲኖረው አድርጎ በመጠቀም ረገድ ያለውን ባሕል ለማበረታታት በሌላ በኩል ደግሞ ለሰው ልጅ ሕይወት ከፍ ያለ ዋጋ ሰጥቶ ማለፉን የሚያረጋግጥ ይመስላል።

በሀገራችን የወንጀል ሕግ የሰው ግድያ ወንጀል በአራት ተከፍሎ የተቀመጠ ሲሆን እነዚህም ከባድ የሰው ግድያ፣ ተራ የሆነ የሰው ግድያ፣ ቀላል የሆነ የሰው ግድያ እና በቸልተኝነት ሰውን መግደል ናቸው። ከእነዚህ ከአራቱ ወንጀሎች በአንዱ የተሳተፈ እና ሰውን የገደለ ሰው ከፍርድ ቤት ቅጣት በተጨማሪ ይህንን

> **ሊደበድብህ ዱላ ይዞ የመጣን ሰው የሰዎችን ርዳታ ወይም የሕግ ድጋፍ ልታገኝ በማትችልበት ሁኔታ እና ልትሸሽ በማትችልበት ሁኔታ አግኝቶህ ራስህን ለማዳን በዱላ ብትደበድበው ወይም ብትመክተው ራስን የመከላከል ድርጊት ስለሚሆን ምንም አማራጭ አጥተህ የፈጸምከው መሆኑ በፍርድ-ቤት ከተረጋገጠ ከወንጀል ቅጣት አያስጥልም**

ነፍሰ-ገዳይነት የሚለውን ስያሜ የመሸከም ኃላፊነት አለበት። ሌላው ቀርቶ በመንገድ ትራፊክ አደጋ ሰው መግደልም ነፍሰ ገዳይ የሚያስብል ነው::

ከባድ የሰው ግድያ በሕጉ አንቀፅ 539 የተቀመጠ ሲሆን ግድያን ከባድ ግድያ የሚያደርጉ በርካታ ምክንያቶች ያሉ ሲሆን በዋናነት ግን መመዘኛው ወንጀሉን ለመፈፀም ከነበረ የሀሳብ መጠን እና ወንጀል ለመፈፀም ካለ ከፍተኛ ፍላጎት ጋር የተያያዘ ነው። ወንጀሉን ለመፈጸም አጥብቆ መፈለግ፣ ቀድሞ ማሰብ ወይም አፈፃፀሙን ጨካኝ ማድረግ በዋናነት ግድያን ከባድ ግድያ ያደርገዋል።

ይህንን ወንጀል የሚፈጽሙ ግለሰቦች ወንጀል ለመፈፀም ከፍ ያለ ፍላጎት አላቸውና ከወንጀል ፍትሕ አንፃር የአደገኛ ሀሳብ ባለቤቶች ናቸው። በመሆኑም ሕጉ በዛው መጠን ወንጀሉን የፈፀመውን ግለሰብም ይሁን ሌሎችን ለማስተማር የሚችል፤ ወንጀል የመሥራት ሀሳብን ሊቀጣ የሚችል ከባድ ቅጣት ይጥልበታል።

ከባድ የሰው ግድያ ወንጀል በእድሜ ልክ ፅኑ እሥራት ወይም በሞት ያስቀጣል። የጥንታዊ የሀሙራቢ ሕግ ብልጭታን በከፊል በዚህ ጉዳይ ልንመለከተው እንችላለን። ዓይን ላጠፋ ዓይን እንደሚባለው የሰው ሕይወትን በከባድ ግድያ ላጠፋ ሰው ሁኔታዎች ተሟልተው በተገኙ ጊዜ የእሱ ሕይወትም እንዲጠፋ ፍርድ ሊሰጥበት ይችላል።

ተራ የሰው ግድያ የሚባለው በሕጉ አንቀፅ 540 ስር የተመለከተ ሲሆን በድንገተኛ ፀቦች ወይም ግጭቶች መካከል የሚፈፀሙ ከባድም ቀላልም ያልሆነ የሰው ግድያ ወንጀሎች የሚታዩበት ድንጋጌ ነው። ይህ ወንጀል በአብዛኛው ጊዜ የሚፈፀመው በማይተዋወቁ ሰዎች፤ ቀድሞ ፀብ በሌላቸው ሰዎች መካከል በተለያዩ አጋጣሚዎች ነው።

ዓቃቤ ሕግ በነበርኩበት ጊዜ ከማስታውሳቸው በዚህ አንቀፅ ስር ከተዳኙ ጉዳዮች መካከል አንዱ መጠጥ ቤት ውስጥ ገዳይ ሟችን “ከእኔ ጋር ቀድማ ከደነሰች ሴት ጋር ለምን አብረህ ደነስክ፣ ንቀኸኝ ነው” በሚል ፀብ የተነሳ ሟችን ጠርሙስ ሰብሮ በተለያዩ ቦታዎች ሟችን በመውጋት ሕይወቱ እንዲያልፍ ያደረገበት መዝገብ የማረሳው ነው። በወንጀል ፍትሕ አስተዳደር ውስጥ በቆየሁበት ጊዜ የተመለከትኩት በዚህ የግድያ ወንጀል የሚሳተፉ ሰዎች አብዛኞቹ ከወንጀሉ ድርጊት በኋላ ወዲያውኑ በከፍተኛ ፀፀት ስር የሚወድቁ ናቸው።

ከባድ የግድያ ወንጀል የሚፈፅሙ ሰዎች የቀደመ ዝግጅት የሚያደርጉ፤ አስበው እቅድ የሚይዙ ውጤቱንም ከሞላ ጎደል የሚቀበሉ የወንጀል ሀሳብ የሚያመዝንባቸው ሰዎች ናቸው። ቀጥለን እንደምናየው በቀላል ግድያ ወንጀል የሚሳተፉ ሰዎች ደግሞ በተወሰነ ደረጃ ገፊ ምክንያቶች አሏቸው። በተራ የሰው ግድያ ወንጀል የሚገቡ እና ይህንን ወንጀል የሚፈፅሙ ሰዎች ግን በቅፅበት እልህ፣ ትዕግስት ማጣት፣ አልደፈርም ባይነት....ወዘተ በመሳሰሉ የስሜት ሚዛን መጓደል ወንጀሉን የሚፈፅሙ በመሆኑ ወዲያውኑ በከፍተኛ ፀፀት ውስጥ ይወድቃሉ::

በዚህ ወንጀል ውስጥ ከመውደቅ የሚጠቅመን ትልቅ ባሕሪ ትዕግስት ነው። ጊዜያዊ ግጭት ከታገስነው እና ከተውነው ወይም በሠላም ከፈታነው ወዲያውኑ የሚያልፍ ሲሆን ለምን ተነካሁ በማለት ከገባንበት ደግሞ ራስንም ሌላን ሰውም የሚጎዳ ውጤት ይዞ የሚመጣ ይሆናል። በተለይም በምሽት መዝናኛ ቤቶች አካባቢ በፍፁም ፀብ ውስጥ እንዳይገቡ ፀሐፊው ይመክራል። በወንጀል ሕጋችን መሠረት ይህንን ወንጀል የፈፀሙ ሰዎች እንደ ሁኔታው እና እንደ አፈፃፀሙ ከአምስት ዓመት እስከ ሃያ ዓመት በሚደርስ ፅኑ እሥራት ይቀጣሉ::

ሦስተኛው የግድያ ዓይነት ቀላል የሆነ የሰው ግድያ ሲሆን በሕጉ አንቀፅ 541 ስር የሚዳኝ ነው። በዚህ ስር የሚወድቁ ግድያዎች መነሻቸው አስገዳጅ የሆኑ ምክንያቶች ወይም ድርጊቱን የሚፈፅመውን ሰው ሞራል የሚፈትኑ ፅኑ ምክንያቶች ናቸው። ለምሳሌ ራስን ለመከላከል ወደ ፀብ የገባ ሰው የወሰደው እርምጃ ራስን ለመከላከል ከሚያስፈልገው የምጣኔ ምዘና በላይ ሆኖ ሰው ከሞተበት በዚህ ድንጋጌ ስር ይቀጣል።

ሊደበድብህ ዱላ ይዞ የመጣን ሰው የሰዎችን እርዳታ ወይም የሕግ ድጋፍ ልታገኝ በማትችልበት ሁኔታ እና ልትሸሽ በማትችልበት ሁኔታ አግኝቶህ ራስህን ለማዳን በዱላ ብትደበድበው ወይም ብትመከተው ራስን የመከላከል ድርጊት ስለሚሆን ምንም አማራጭ አጥተህ የፈጸምከው መሆኑ በፍርድ-ቤት ከተረጋገጠ ከወንጀል ቅጣት አያስጥልም። ነገር ግን ይህንን ዱላ ይዞ የመጣን ሰው መሣሪያ ተኩሰህ ብትገድለው ከተፈቀደልህ የመከላከል መጠን አልፈኃልና በቀላል የሆነ የሰው ግድያ ወንጀል ያስከስስሃል። እንዲህ ዓይነት ሁኔታዎች በዚህ ድንጋጌ ስር ይታያሉ::

ሌላው የዚህ ግድያ ዓይነት የሚሸፍናቸው ጉዳዮች ከሰው ልጅ ሚዛናዊ የሞራል ሁኔታ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ናቸው። ለምሳሌ አንድ ባለትዳር የሆነ ሰው የሕግ ሚስቱ ከሌላ ወንድ ጋር “ተኝታ” ቢያገኛት እና የግድያ ወንጀል በአንዳቸው ላይ ቢፈፅም ከፍ ያለ ደም የሚያፈላ ምክንያት በመሆኑ የግድያው ዓይነት በዚህ ድንጋጌ ስር የሚታይ ይሆናል። ቀላል የሰው ግድያ ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እሥራት ይቀጣል::

የመጨረሻው በቸልተኝነት ሰው መግደል ሲሆን ይህም በዋናነት ከጥንቃቄ ጋር የተያያዙ ችግሮችን የሚቀጣ ሕግ ነው። በተለይም የሌላ ሰውን ሕይወት፣ ጤንነት ወይም ደህንነት የመጠበቅ የሙያ ወይም ሌላ ግዴታ ያለባቸው እንደ ሕክምና ባለሙያዎች ወይም አሽከርካሪዎች ከጥንቃቄ ጉድለት በሰው ሕይወት ላይ ወንጀል በፈጸሙ ጊዜ እንደ ነገሩ ሁኔታ ከአንድ ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት ድረስ ሊቀጡ ይችላሉ።

ይህም ሁኔታ በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 543 ስር ባሉት ንዑስ ድንጋጌዎች የሚታይ ነው። በቸልተኝነት ሰው መግደል ታዲያ ሁልጊዜ ባለሙያዎችን ብቻ የሚመለከት አይደለም። አንዳንድ ጊዜ በተለይም በገጠሩ አካባቢ ልጁን ለመቅጣት ሲል ያልተገባ ወይም ያልተመጣጠነ ኃይል ተጠቅሞ ልጁን የሚገድል ወላጅ ያጋጥማል። እነዚህ እና መሰል ጉዳዮችም በቸልተኛነት ሰው መግደል የሚያስቀጡ ናቸው።

በአጠቃላይ የወንጀል ሕጉ በእነዚህ አራት የግድያ ዓይነቶች በሰው ሕይወት ላይ ወንጀል የሚፈፅሙ ሰዎችን ይቀጣል። በሕጉም ነፍሰ-ገዳይ ተብለው ይታወቃሉ። ከዚህ የሕጉ ስያሜ እና ቅጣት መገንዘብ የሚገባን መሠረታዊ ጉዳይ ሁልጊዜም ቢሆን ከግድያ ወንጀል ፈፅሞ መራቅ እንደሚገባን እና በየትኛውም ሁኔታ ይህንን ወንጀል ከመፈፀም መቆጠብ እንደሚገባን ነው። የራሳችንን ሕይወት በምንወደው ልክ ለሌሎች ሰዎች ሕይወትም ተገቢውን ዋጋ መስጠት ሰብዓዊነት እና ዘመናዊነት መሆኑን ተገንዝቦ፤ ፈታኝ ሁኔታዎች በሚያጋጥሙ ጊዜያት እንኳን ሌሎች አማራጮችን ተጠቅሞ በማሳለፍ ይህንን ወንጀል መፀየፍ ይገባል።

**ክብር ለሰው ልጅ ሕይወት !**

**አመሰግናለሁ::**

ኢኮኖሚ

# ግብርና

# የግብርና ምርትና ምርታማነትን የማሳደግ ጥረት - በሐረሪ ክልል

**በኃይሉ አበራ**

በሀገሪቱ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ፣ ለአግሮ ኢንዱስትሪዎች ግብዓት እንዲሁም ለውጭ ምንዛሪ ግኝት ያለውን ፋይዳ ታሳቢ በማድረግ ለግብርናው ዘርፍ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሠራ ነው። ለእዚህም እንደማዳበሪያ ያሉ ግብዓቶችን በስፋት በማቅረብ፣ ለሜካናይዜሽን እርሻ ምቹ ሁኔታ እንደሚፈጥር የታመነበትን ኩታ ገጠም እርሻን እንዲሁም ሜካናይዜሽንን በማስፋፋት፣ ግብርናውን ከመኸርና በልግ በተጨማሪ በመስኖ ልማትም በመደገፍ ሰፋፊ ሥራዎች እየተሠሩ ናቸው።

ይህን ሁሉ ተከትሎም የዘርፉ ምርትና ምርታማነት በየዓመቱ እየጨመረ ይገኛል። ይህን ምርታማነት ለማሳደግ የሚደረገው ጥረት አሁንም ተጠናክሮ ቀጥሏል። በዚህ ልማት ሁሉም ክልሎች በስፋት እየሠሩ ይገኛሉ።

በዛሬው የግብርና ዓምዳችን የሐረሪ ክልል በግብርናው ዘርፍ በተለይ በተያዘው የመኸር ወቅትና መስኖ ልማት ላይ እያከናወነ ያለው ሥራ ዳሰናል። ክልሉ በተለይ ከሀረማያ ዩኒቨርሲቲ፣ ከኦሮሚያ ክልል ግብርና ቢሮ እንዲሁም ከግብርና ሚኒስቴር እና ከሌሎች ተቋማት ጋር በመቀናጀት የክልሉን የግብርና ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ፣ ለወጣቶች የሥራ ዕድል ለመፍጠር እየሠራ ነው።

የሐረሪ ክልል ምክትል ፕሬዚዳንት እና የክልሉ የግብርና ቢሮ ኃላፊ ወይዘሮ ሮዛ ዑመር እንዳብራሩት፤ በክልሉ በ2016/17 የምርት ዘመን 11,774 ሄክታር ለማረስ ታቅዶ ሙሉ 100% ታርሷል። ከዚህም 800 ሄክታር ማሽላ 450ሄክታር ሰንዴ ኢኒሺየቲቭ ነው። በዚህም በክልሉ ሁለት ክላስተር የሚገኝ ሲሆን፤ አንደኛው 450 ሄክታር የስንዴ ክላስተር ነው፤ ሁለተኛው ደግሞ 350 ሄክታር የማሽላ ክላስተር እርሻ ነው። በክልሉ በስፋት የሚታወቁት የግብርና ምርቶች ማሽላ፣ በቆሎ፣ ለውዝ እና ስንዴ ናቸው።

ከዚህ 11,774 ሄክታር መሬት ውስጥ በኢኒሺየቲቭ የታረሰውን በተለየ መንገድ እንዲለማ ተደርጓል። ይህም የግብርና ቢሮ ባደረገው እገዛ የተሠራ ነው። አንዱ ኢኒሺየቲቭ የማሽላ ኢኒሺየቲቭ ሲሆን፣ ይህም በሀረማያ ዩኒቨርስቲ የተደረገውን ጥናት በመውሰድ የተዘራ ነው። ይህ የማሽላ ዝርያ ምርት በሦስት ወር ይደርሳል፤ ይህ አዝመራ ደርሶ ተሰብስቧል።

በክልሉ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ እየለማ ያለው ነባሩ የማሽላ ዝርያ ምርት ለመስጠት ከሰባት ወር እስከ ዘጠኝ ወር እንደሚወስድበት አስታውቀው፣ በሄክታር የሚያስገኘውም 13 ኩንታል ብቻ ነበር ብለዋል። በምርምር ተገኝቶ እንዲለማ የተደረገው የማሽላ ዝርያ በሦስት ወር ምርት የሚሰጥ እንደሆነ አመልክተው፣ በሄክታር ከ42 እስከ 45 ኩንታል እንደሚገኝበትም ገልጸዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ የዚህ ማሽላ ዝርያ ጠቀሜታው ብዙ ነው፤ አንዱ ጠቀሜታው በፍጥነት መድረሱ ነው፤ ማሽላን በአነስተኛ መሬት ላይ ዝናብ በመጠበቅ ብቻ እንዲለማ የሚደረግ ከሆነ ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ አይቻልም። በክልሉ ያለው መሬት አነስተኛ ነው። አዲሱ የማሽላ ዝርያ በዓመት ሦስት ጊዜ ለማምረት እንደሚያስችል ጠቅሰው፣ ይህን የማሽላ ዝርያ ከማኅበረሰቡ ጋር እንዲላመድ እና በክላስተርም እንዲለማ እየተደረገ መሆኑን ወይዘሮ ሮዛ አስታውቀዋል።

በአሁኑ ጊዜም በዘር ከተሸፈነው 800 ሄክታር መሬት ላይ 36 ሺህ ኩንታል ምርት መሰብሰቡን አስታውቀዋል። በተወሰኑ ወረዳዎች በተለመደው የማሽላ ዝርያ በዘር የተሸፈነው ማሳ ምርት ገና እንዳልደረሰ አስታውቀዋል። የቢሮ ኃላፊዋ ምርት በተሰበሰበበት መሬት ላይ የበጋ መስኖ ተግባራዊ ለማድረግ ዝግጅቱ መጠናቀቁን ገልጸዋል፤ አራት ሺህ 700 ሄክታር መሬት ላይ በበጋ መስኖ ለማምረት እየተሠራ መሆኑን አመላክተዋል።

ከአየር ንብረት ጋር በተያያዘ የደረሰ ሰብልን በወቅቱ ለመሰብሰብ ማሽነሪዎችን ለመጠቀም ምን ያህል ተሠርቷል በሚል ለቀረበላቸው ጥያቄ ሲመልሱም፣ ቴክኖሎጂው ጥቅም ላይ እንደሚውል ተናግረዋል። የማሽላና የስንዴ ማሽነሪ ለየብቻ መሆኑን ጠቅሰው፣ ይህም ጥቅም ላይ እንዲውል የተደረገው ምርት ለመሰብሰብ ሳይሆን ለመውቃት ነው ብለዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ በኦሮሚያ ክልል የሚገኘው የግብርና ምርምር ማዕከል በቴክኖሎጂ ምርምር ላይ ይሠራል፤ ክልሉ ማሽላን የሚወቁ ማሽነሪዎችን ለሦስት ወረዳዎች ከምርምር ማዕከሉ ገዝቶ አቅርቧል። ይህም ሰብሉን በተሻለ መንገድ ለመውቃት ያስችላል። ቴክኖሎጂው ሥራ ላይ መዋሉ አርሶ አደሩ ድካም ሳያጋጥመው በማሽነሪው በመውቃት ምርቱን እንዲሰበስብ አስችሎታል። ስድስት ማሽነሪዎች ተገዝተው ሦስቱን ማስተላለፍ ተችሏል። መግዛት ለሚችሉት ወረዳዎችም ስለቴክኖሎጂው ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማድረግ ላይ እየተሠራ መሆኑን አስታውቀዋል።

የቢሮ ኃላፊዋ እንዳሉት፤ ቴክኖሎጂ ከመጠቀም ጎን ለጎን ኅብረተሰቡን በማወያየት፣ የመንግሥት ሠራተኛውን፣ የፀጥታ አካሉን /በአካባቢው የሚገኘውን የምሥራቅ ዕዝ./ በማስተባበር ምርት በጊዜ እንዲሰበሰብ ተደርጓል። በዚህም በአካባቢው ተከስቶ የነበረው ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ በአዝመራ ላይ ጉዳት ሳያስከትል በፍጥነት መሰብሰብ ተችሏል።

በክላስተር የተገኘው ምርት በመጀመሪያ ደረጃ ለምርጥ ዘርነት እንደሚፈለግ ተናግረው፣ በዚህም ምርጥ ዘር ወደ አልተደረሰባቸው አርሶ አደሮች ለማዳረስ እየተሠራ ነው ይላሉ። የክልሉ ግብርና ቢሮ ይህንን ምርት ለአርሶ አደሩ ለማድረስ ከፍተኛ ግዢ አድርጓል ሲሉም ጠቅሰው፣ ክልሉ የገዛውን የማሽላ ምርጥ ዘር አንድ ቦታ በማሰባሰብ ላይ መሆኑን ጠቁመዋል። ይህ ምርት ከአርሶ አደሩ ሲገዛ በቁጠባ እንዲጠቀም እየተደረገ ነው ብለዋል።

የክልሉ ግብርና ቢሮ ለዘር እና ይህን ዘር ወደ ሌሎች አርሶ አደሮች ለማስፋፋት ምርቱን ሲገዛ ምርቱን የሸጠው አርሶ አደር ገንዘቡን እንዳያባክን ለማድረግም በባንክ እንዲቆጥብ እየተደረገ መሆኑን ገልጸዋል። ለምግብ የሚያዘጋጀው እንዲሁም ለማኅበረሰቡ በቀጣይ በዚህ መሬት የሚዘራውን ምርጥ ዘር በተመሳሳይ እንዲቆጥብ በሚያስችለው ላይ ሥልጠና ተሰጥቷቸዋል።

በልማታዊ ሴፍቲኔት የሚጠቀሙ አርሶ አደሮችን በተመለከተም ሲያብራሩ፣ በዚህም በሴፍቲኔት እገዛ ውስጥ የቆዩ አንድ ሺህ 200 አርሶ አደሮች በዚህ ዓመት ማብቃት የተቻለ መሆኑን አስታውቀዋል። ለሴፍቲኔት ተጠቃሚዎችን በተመለከተም ሲያብራሩ እንደገለጹት፤ በመጀመሪያ ደረጃ ውሃ እንዲያቁሩ በማድረግ የታቆረውን ውሃ በፓምፕ በመጠቀም እና ሦስት ጊዜ በላይ እንዲያመርቱ ለማስቻል እየተሠራ ነው።

ለእዚህም በድጋፍ እና በግዢ የቀረቡ ወደ 150 ፓምፖች ለሴፍቲኔት አርሶ አደሮች እንዲሰራጩ መደረጋቸውን አመላክተዋል። ውሃ የሚጠራቀምበት ሸራ እንዲሰራጭ በማድረግ 1200 አርሶ አደሮች በዚህ ዓመት ከሴፍቲኔት ድጋፍ ራሳቸውን እንዲችሉ ለማድረግ መታቀዱን ገልጸው። በሶላር እና በሙብራት የሚሠራውንም ፓምፕ ከተለያዩ ፕሮጀክቶች ጋር በመሆን እንዲጠቀሙ ማድረግ እንደተቻለም ጠቅሰው፣ በዚህ መልኩ ራሳቸውን እንዲችሉ የተደረጉ ቤተሰቦች ወደ ምርታማነት የማሸጋገር ሥራ ላይ ሰፊ ሥራዎች እየተሠሩ ናቸው ይላሉ።

በሌላ በኩል በክልሉ በሌማት ትሩፋት የተሠሩ ሥራዎችን አስመልክተው ወይዘሮ ሮዛ ዑመር እንዳብራሩት፤ የክልሉ ግብርና ቢሮ በእንስሳት እርባታ በተለይ የተዳቀሉ የተሻሻሉ እንስሳትን ዝርያ ቴክኖሎጂን በማስደገፍ በማዳቀል ዘዴ የወተት እንስሳት ምን ያህል ምርት መስጠት ይገባቸዋል በሚለው ላይ ተሠርቷል። በዚህም የወተት መንደር በሚል 17 ቀበሌዎችን በመለየት እያንዳንዱ ቤተሰብ ቢያንስ ከሁለት እስከ አምስት የወተት እንስሳት ሊኖረው ይገባል በሚል እየተሠራ ይገኛል። እስካሁን ከ17 ቀበሌዎች በ15 ቀበሌዎች ላይ ሙሉ ፓኬጅ ማከናወን ተችሏል።

በእንስሳት ማርባት ሥራ ላይም ትልቅ የናይትሮጅን ማሽን መኖሩን ጠቁመው፣ በማዳቀል ሥራ ጊደሮችን በማዳቀል ለእርድ ብቻ ሳይሆን ጥጃ መስጠት በምትችል ደረጃ ከሀረማያ ዩኒቨርስቲ ጋር እየተሠራ መሆኑን አመላክተዋል። ለእዚህም የእንስሳት ሐኪሞች እንዳሉም ጠቅሰው፣ በዚህ ሥራ በልዩ ትኩረት ትልቅ በጀት ተመድቦ እየተሠራ ነው ብለዋል።



የሐረሪ ክልል ምክትል ፕሬዚዳንት እና የክልሉ የግብርና ቢሮ ኃላፊ ወይዘሮ ሮዛ ዑመር

እንደ እሳቸው ገለጻ፤ የዶሮ እርባታን በተመለከተም ለሁሉም አርሶአደር እናቶች በየቤቱ 25 ዶሮዎች ይሰጣሉ። እነዚህ እናቶች 25 ዶሮዎችን ሲወስዱም እኛ የምናረባቸው ዶሮዎች እና የግል ዶሮ አርቢዎች የሚያረቡዋቸው ልዩነት አላቸው። ልዩነታቸውም የግል አርቢዎች እንቁላል መጣል ብቻ እንጂ እንቁላላቸው መልሶ ጫጩት መሆን አይችልም።

በክልሉ ግብርና ቢሮ በሌማት ትሩፋት ፕሮግራም የሚረቡት ዶሮዎች ግን እንቁላላቸው መልሶ ጫጩት መሆን የሚያስችል ቴክኖሎጂን በመጠቀም የሚታገዝ ነው። እንቁላላቸው መልሶ ጫጩት መስጠት የሚያስችሉ 25 ዶሮዎችን በክልሉ ካሉት ዘጠኝ ወረዳዎች ለሁለቱ ወረዳዎች ማዳረስ ተችሏል። መግዛት የሚችሉ ቤተሰቦች ደግሞ መግዛት እንደሚችሉ ሙሉ ተስፋ በመስጠት እየተሠራ ነው።

በሌላ በኩል የተጠራቀመ ውሃ በተዘጋጀባቸው ቦታዎች ከሀረማያ ሐይቅ ላይ የዓሣ ጫጩት በማምጣት በየቀበሌው በምን መልኩ ውሃ በማጠራቀም አልያም የተጠራቀመ ውሃ ካለበት ስፍራ በሞተር ውሃ በማውጣት በተጠራቀመ ውሃ ዓሣን ማራባት እንደሚቻል ሥልጠናዎች ተሰጥተዋል። በዚህ መልኩም ዓሣን የማርባት ሥራ እየተሠራ ነው።

በተመሳሳይ በክልሉ የማር መንደር እንዳለም ገልጸዋል። ሁለት ሄክታር መሬት ክላስተር በማድረግ ቀፎዎችን አንድ ቦታ ላይ በማሰባሰብ ወጣቶችን በዚህ ላይ በማደራጀት እየተሠራ ነው ብለዋል። በተለይም ከዩኒቨርሲቲ ተመርቀው ለወጡ ወጣቶች ሰፊ የሥራ ዕድል ከመፍጠር ጋር በተያያዘ ለወጣቶቹ የተወሰነ መነሻ ገንዘብ በመስጠት፣ የመሥሪያ ሼድ በመሥራት በዚህ ላይ እንዲሰማሩ ተደርጓል ሲሉ አብራርተዋል። በእነዚህ ሼዶች ያመረቱትን የማር ምርት መሸጥ እንዲችሉና ራሳቸውም እየተጠቀሙ የማኅበረሰቡንም ገበያ ለማረጋጋት እንዲሠሩ እየተደረገ መሆኑን ገልጸዋል። የገበያ ትስስር በማድረግም የቅዳሜ እና እሁድ የሰንበት ገበያ በሚል የማር ምርታቸውን የሚሸጡባቸው የገበያ መዳረሻዎች ተዘጋጅተዋል ሲሉም ጠቁመው፣ በዚህም የዋጋ ንረትን በማረጋጋት ላይ እየተሠራ መሆኑን ወይዘሮ ሮዛ አስረድተዋል።

ከሌማት ትሩፋት ሥራው ጋር በተያያዘ እንደ ችግር ያጋጠመው እና ከእንስሳት መኖ፣ ከዶሮ መኖ ጋር ተያይዞ ያለው ችግር መሆኑን ጠቅሰው፣ የዶሮ መኖ ችግር በዚህ ዓመት መፍታት መቻሉንም አስታውቀዋል።

እሳቸው እንዳብራሩት፤ የመኖ ማቀነባበሪያ ማሽን በመግዛት በዶሮ ማርቢያው አካባቢ ተተክሏል። መኖውም እዛው ይመረታል፤ በግል ዶሮ የሚያረቡ ወጣቶችንም በቢሮው በኩል ያለው የዶሮ ማርባት አሠራር ላይ እየተሠራ ነው። በመጀመሪያ ደረጃ የዶሮ መኖ ከቢሾፍቱ ተጭኖ ይመጣ ነበር። ይህ ሲሆን ዋጋውና የትራንስፖርት ወጪው ከፍተኛ በመሆኑ እንቁላሉንና ዶሮውን በተፈለገው ፍትሐዊ ዋጋ መሸጥ አልተቻለም ነበር። በመሆኑም የዶሮ መኖን እዚሁ ማምረት ይገባል በሚል የማቀነባበሪያ ማሽኑን በመግዛት ወደ ተግባር ተገብቷል ብለዋል።

አሁን ላይ የሐረሪ ግብርና ቢሮ ከሱሉልታ ከሚመጣው የእንስሳት መኖ ጋር በተያያዘ ችግር ያጋጠመው መሆኑን አመላክተዋል። ዋጋውም ከትራንስፖርት ወጪ ጋር በተያያዘ ከፍተኛ መሆኑን ጠቁመዋል። ለእዚህ በመፍትሔነት የተወሰደው ከሐረር ቢራ ፋብሪካ ጋር የእንስሳት መኖውን ማግዛዝ በሚቻልበት ሁኔታ ላይ ስምምነት በመፈራረም እየተሠራ ነው።

የረጅም ጊዜው መፍትሔ ደግሞ የእንስሳት መኖ ማቀነባበሪያ እዚህ ማቋቋም መሆኑን ጠቁመው፣ ለእዚህም ከግብርና ሚኒስቴር ጋር በመነጋገር እየተሠራ መሆኑን አስታውቀዋል። በእንስሳት መኖ እና በዶሮ መኖ ላይ ችግር ከማጋጠሙ በስተቀር በክልሉ የሌማት ትሩፋት ሰፋፊ ሥራዎች እየተሠሩ መሆናቸውን ወይዘሮ ሮዛ ዑመር አስታውቀዋል።

# ወቅታዊ

# ‹‹የባሕር በር ጥያቄ ቀጣናውንም ሊቀይር የሚችል ትልቅ ጥያቄ ነው››

- ዳርእስከዳር ታዬ (ዶ/ር)
- በውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩት የአውሮፓና የአሜሪካ ጉዳዮች ዳይሬክተር

ምሕረት ሞገስ

**ኢትዮጵያ በውጭ ግንኙነት ፖሊሲዋ ለጎረቤት ሀገራት ልዩ ትኩረት ትሰጣለች። ይኸው ፖሊሲም ኢትዮጵያ በቀጣናው ላይ ያላትን ተሰሚነት የሚያጎለበት እና ቀጣናውንም በማስተሳሰር ያላትን ሚና በአግባቡ እንድትወጣ የሚያስችላት ነው፡፡**

**ይህንኑ መነሻ በማድረግ የባሕር በርን በተመለከተ ኢትዮጵያ እየሄደች ያለችበትን መንገድ እንዴት ይታያል? የባሕር በር ለማግኘት እየተደረጉ ያሉ ጥረቶች ምን መልክ አላቸው? የሚሉ ጥያቄዎችን በማንሳት በውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩት የአውሮፓና የአሜሪካ ጉዳዮች ዳይሬክተር እና የኢትዮጵያ ፖለቲካ ተንታኝ ዳርእስከዳር ታዬ (ዶ/ር) ጋር ቆይታ አድርገናል። መልካም ንባብ፡-**



ፎቶ፡- ሀዲስ አብርሃ

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያ ለጎረቤት ሀገራት ለምን የበለጠ ትኩረት ሰጠች?**

**ዳርእስከዳር (ዶ/ር)፡-** በአብዛኛው ሀገራት በውጭ ግንኙነት ፖሊሲያቸው ለሀገራት በተለያዩ ምክንያቶች ቅድሚያ ይሰጣሉ። ልዩነቱ ምናልባትም የቅርብና የሩቅ ጎረቤት በሚል መከፋፈል ይቻላል። ያም ሆኖ ለጎረቤት ሀገር ቅድሚያ መስጠት ያስፈልጋል። ለዚህም ጂኦግራፊው ያስገድዳል።

ከሩቅ ካሉ ሀገራት ጋር ምናልባትም በተወሰኑ ጥቅሞች ጉዳይ መገናኘት ሊኖር ይችላል። ነገር ግን ከቅርብ ጎረቤት ጋር የሚኖረው የግንኙነት አድማሱ በጣም ሰፊ ነው። ይህም ማለት በሆነ ጉዳይ ላይ ብቻ እንገናኝ ማለት አይቻልም። ለአብነትም ኢትዮጵያ እና ኢምሬት በጂኦግራፊያዊ አቀማመጣቸው ጎረቤት አይደሉም። ስለዚህ ግንኙነት ሊመሠርቱ የሚችሉት በተመረጡ ጉዳዮች ላይ ብቻ ነው።

ኢትዮጵያ ከኤርትራ እና ከሶማሊያ ጋር የሚኖራት ግንኙነት እንደሌሎች ሀገራት አይሆንም። ምክንያቱም የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት አለ። የማንነት ተመሳሳይነት ይኖራል። ጎረቤት በመሆን ብቻ ሕጋዊና ሕገወጥ የንግድ ግንኙነት ይፈጠራል። ድንበር በጋራ ማስተዳደርም አለ።

ሌላው ከጎረቤት ሀገር ጋር ግንኙነት የሚመሠረተው በመምረጥ አይደለም። ነገር ግን ከሌሎች ሀገራት ጋር ግንኙነት የሚመሠረተው በምርጫ ነው። ለአብነት ከመካከለኛው አፍሪካ ሀገራት ከየትኞቹ ጋር መጠቃቀም እንችላለን ብሎ መምረጥ ይቻላል። ጎረቤት ሀገር ጋር ሲመጣ ግን በዚህ መንገድ መምረጥ አይቻልም። በዚህ መሠረት የኢትዮጵያ ፖሊሲ ከ2010 ወዲህ ለጎረቤት ሀገራት ትኩረት የሰጠ ነው ሲባል፤ በብዙ ሥራዎቻችን ቅድሚያ ለጎረቤት እንሰጣለን ማለት አንደኛው ሲሆን፤ ሁለተኛ ደግሞ ከሁሉም ጎረቤት ሀገራት ጋር መልካም ግንኙነት ለመመሥረት ጥረት ይደረጋል ማለት ነው።

ከለውጡ አስቀድሞ በነበሩ ዓመታት ኤርትራን በጠላትነት የማቆየት ስትራቴጂ ነበር። ከሶማሊያና ከኬንያ ጋር ስንገናኝም ሁልጊዜ ይህን ታሳቢ ያደረገ ግንኙነት ነበር። ጎረቤት ተኮር እናድርገው ሲባል ግን፤ ሁሉንም ጎረቤት ሀገራት በተቻለ መጠን ወደ አንድ ማምጣት የሚችል ፖሊሲ ከሁሉም ጋር በሠላም መኖርን ታሳቢ ያደረገ ነው፡፡

ጎረቤት ተኮር ፖሊሲ በአፍሪካ ቀንድ ላይ ያለው ሌላ ትርጉም አንዱ በሌላ ሀገር የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ መግባት፤ አንዱ የሌላ ሀገርን ተቃዋሚ ኃይል ማሠልጠን፤ ማስታጠቅና መሰል ልምዶች ላለፉት 50 እና 60 ዓመታት ነበሩ። ከ1960 ዎቹ ጀምሮ ከዚህ የተነሳ በኢትዮጵያና በጎረቤት ሀገራት መካከል ያለው ግንኙነት አንድ ጊዜ ሞቅ ሌላ ጊዜ ደግሞ ቀዝቀዝ እያለ እንደየወቅቱ ሁኔታ የሚቀያየር ነው። ለምን? ቢባል አንዱ በአንዱ ጉዳይ ጣልቃ መግባት የተለመደ ነው።

ቀላል ምሳሌ ብናነሳ በቅርቡ የኤርትራው ፕሬዚዳንት በሰጡት ቃለምልልስ ብዙ ሰዓት ስለኢትዮጵያ ሲያወሩ ተደምጠዋል። እንደዚህ ዓይነት ነገሮች ነበሩ፤ አሁንም አሉ። አሁን ላይ የተለወጠው ነገር እኛ በጎረቤት ሀገር ጉዳይ እጃችንን አናስገባም። በመፈቃቀድና በመተባበር ካልሆነ በስተቀር በሚል የፖሊሲ እይታ ለውጥ ተከስቷል። ሌላው ጎረቤት ሀገርን በተመለከተ የሠላም ተዋናይ መሆን የሚል አንድምታ አለ። ለአብነትም ገና ‹‹ሀ›› ብሎ ለውጡ ሲመጣ ሱዳን ከአልበሽር መወገድ ጋር ተያይዞ በሲቪሊያኑና በወታደራዊ ኃይል መካከል አለመግባባት ሲፈጠር የማደራደር ሥራዎች ተሠርተዋል።

በኢትዮጵያ፣ በሶማሊያና በኤርትራ መካከል ወደአንድነት የመምጣት ፍላጎት ሲታይ እና በዚህም ጅቡቲ ስትቀየም የመዳኘት ሥራዎች ሲሠሩ ቆይተዋል። ይህ የሚያሳየው በመጀመሪያ ደረጃ ከጎረቤት ሀገራት ጋር ያለን ችግር መፍታት ነው። ከዚህ ባለፈም ከጎረቤት ሀገራት ጋር ያለን ግንኙነት የሚቃኘው ከኃያልን ሀገራት ጋር ያለንን ግንኙነት መሠረት በማድረግ ነበር። አሁን ላይ ግን ይህ ተቀይሯል። ከጎረቤት ሀገራት ጋር ያለው ጥቅም የሚሰላው በራስ ውሳኔ ነው። ያኔ ቢሆን ኃያላን ሀገራት ምን ይፈልጋሉ? ምን ይላሉ? የሚለውን መሠረት በማድረግ ነበር። ከዚህ አንጻር ለውጥ አለ ማለት ይቻላል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያ በቀጣናው ሠላም እና መረጋጋት እንዲሰፍን እያደረገች ያለውን ጥረት እንዴት ይመለከቱታል?**

**ዳርእስከዳር (ዶ/ር)፡-** እኛ ለጎረቤት ሀገራት ሠላም አስተዋፅዖ እናደርጋለን ስንል የሠላም ጥረቱን የምናደርገው በሰው ሀገር ውስጥ ነው። ይህም የመሳካት ዕድሉ የሚወሰነው በአብዛኛው በዛ ሀገር ፍላጎት ነው። ለአብነት ደቡብ ሱዳንን አደራድራለሁ ወይም ሠላም ለማምጣት እጥራለሁ ሲባል፤ የእኛ ጥረት የእኛ የዲፕሎማሲ አቅምና ተፅዕኖ የመፍጠር ሁኔታ የተወሰነ አስተዋፅዖ አለው። ነገር ግን የሠላም ጥረቱን የሚቀበለው ሀገር ወሳኝ ነው።

ባለፉት ስድስት ዓመታት የታዘብነው ነገር ይህንን ነው። የመጠራጠርና በጠላትነት የመተያየት ሁኔታ ነበር። የጋራ በሆኑ ጉዳዮች ላይ በአንድነት እንሥራ ወደ መተባበር እንምጣ በመደመር አስተሳሰብ አንድ ላይ እንቁም እንበርታ የሚለው አመለካከት ሲመጣ ተመሳሳይ ምላሽ ቢገኝ ጥሩ ነበር።

ሌላው ሠላምን ለማምጣት በምናደርገው ጥረት፤ በአንድ በኩል ሠላምን ለማምጣት ጥረት እናደርጋለን። በሌላ በኩል የራሳችን ፍላጎት አለን። ለጎረቤት ሀገር ሠላም እንደምንሠራው ሁሉ ለእኛ ጥቅም እንሠራለን። ለአብነት የባሕር በር ማግኘት ለኢትዮጵያ መሠረታዊ ፍላጎት ነው። ዓባይ ግድብን መገደብ መሠረታዊ ፍላጎት ነው። ነገር ግን ይህን ስናደርግ ደስ የማይለው ጎረቤት ሀገር አለ። ይህ ደግሞ የሚፈጥረው የራሱ የሆነ ችግር አለ።

በጎረቤት ሀገራት ሠላም ለማምጣት ብዙ ጥረት ተደርጓል። ለአብነት ሱዳን ወደ ጦርነት ከመግባቷ አስቀድሞና ከገባች በኋላም ብዙ ጥረት ተደርጓል። ነገር ግን ሱዳን ላይ ሠላም እናመጣለን የሚሉ ብዙ ተዋናዮች አሉ። ሌሎች በሌላ መንገድ ሲገቡ፤ ከባድ ይሆናል። ደቡብ ሱዳን ላይ ጥሩ ተደማጭነት አለን። በማደራደርም የተሻለ ሠላም እንዲመጣና ግጭቶች እንዲቆሙ በማድረግም ከለውጡ አስቀድሞ የተሠሩ ሥራዎች ስኬታማ ናቸው። ምናልባት ደቡብ ሱዳን ላይ ያለው ችግር ወደ ዲሞክራሲያዊና ወደ ምርጫ ሥርዓት የመምጣት ሂደቱ መጓተት ይታይበታል። ይህ ማለት ሠላም ላይ አልሠራንም ማለት አይደለም፡፡

ሌላው ኤርትራ ላይ የተሠራው ሥራን መጥቀስ ይቻላል። በወቅቱ ቀጣናው ላይ የሠላም ንፋስ እንዲነፍስ አድርጎ ነበር። አዲስ ዓይነት የአፍሪካ ቀንድ እንዲመጣ አድርጎ ነበር። ይሁንና ኋላ ላይ ነገሮች እየተቀየሩ መጥተዋል። ይሁን እንጂ ኢትዮጵያ ለቀጣናው ሠላም ትልቅ ሚና ተጫውታለች። የሚለው ይወሰዳል። መዘንጋት የሌለበት ግን ሁልጊዜ ለጎረቤት ሀገራት ብቻ ተብሎ አይሠራም፤ የራስ ሥራም ይሠራል። ይህም ምን ዓይነት ለውጥ አምጥቷል የሚለው በቀጣይ አብሮ የሚታይ ይሆናል፡፡

**የባሕር በር ጥያቄ ለኢትዮጵያ የግድ የሕልውና ጉዳይ ነው፡፡ ይህንን የምንለው የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ታዳጊ ነው፡፡ ታዳጊ ኢኮኖሚ እና ታዳጊ ሕዝብ አለ፡፡ ይህንን የሚያህል ሕዝብ ይዞ በትንሽዬ ፖርት ላይ፤ ለዚውም በደካማ መሠረተ ልማት በአንድ የባቡር መስመር፤ እየተበላሸ በሚቋረጥ አንድ የአስፓልት መንገድ ላይ ለዘላለም እኖራለሁ ብሎ የሚያስብ ሀገር የለም**

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያ ቀጣናዊ ትስስርን ለማምጣት ምን ያህል እየሠራች ነው?**

**ዳርእስከዳር (ዶ/ር)፡-** ኢትዮጵያ ቀጣናዊ ትስስር ለማምጣት የምትሠራቸው በርካታ ሥራዎች አሉ። ሠላም መፍጠር አንድ ነገር ነው። በተፈጠረው ሠላም ላይ ደግሞ ወደ ተሻለ መንገድ መሄድ ሌላ ጉዳይ ነው። በዚህ መንገድ የሚፈጠር ቀጣናዊ ትስስር ወደፊት በጉልህ ሊወሰድ የሚችልና ትልቅ ስኬት ተደርጎ የሚወሰድ ነው። ምክንያቱም ሠላም ፈጥሮ አብሮ መነገድ ካልተቻለ፤ በጋራ ጉዳዮች ላይ በጋራ መቆም ካልተቻለ፤ ትርጉም የለውም። ለአብነት አሁን ላይ የተጀመሩ ሙከራዎችን ማንሳት ይቻላል።


ኢትዮጵያ የኤሌክትሪክ ኃይል ኢንቨስት ማድረግ ጀምራለች። ይህን የኤሌክትሪክ ኃይል በሠላም ጊዜ ለኬንያ፣ ለሱዳንና ለጅቡቲ ማቅረብ ችላለች። ይህ ማለት ከፖለቲካ ነፃ በሆኑ በእንደዚህ ዓይነት ጉዳዮች በጋራ የሚሠራባቸው ዕድሎች እየሰፉ መጥተዋል። ኢትዮጵያ ከሱዳን ሸንኩርት ሳይቀር ታስመጣለች በጋራ ይነገዳል። ነዳጅም ይመጣል፤ ይህ ትልቅ ዕድል ነው። ይህም ማለት ተቀራርቦና ተነጋግሮ በጋራ የመሥራት ዕድሎች እየጨመሩ ናቸው፡፡

አንዳችን ለአንዳችን ጥገኛ እየሆንን እንሄዳለን ማለት ነው። ስለዚህ የአቅም ግጭት በእነዚህ ሀገራት መካከል ሊመጣ አይችልም። ለአብነትም ከሌሎች ውሃና የኤሌክትሪክ ኃይል ከሚወስዱ ሀገራት ይልቅ ኢትዮጵያና ጅቡቲ የመዋጋት ዕድላቸው ዝቅተኛ ነው። ለምን? እነዚህን ጥቅሞች ላለማጣት ሲባል ችግሮቹን በውይይት የመፍታት

ወደ ገጽ 9 ዞሯል

# «የባሕር በር ጥያቄ ቀጣናውንም…

ከገጽ 8 የዞረ



ዕድል የሰፋ ይሆናል። ከሱዳንና ከኬንያም ጋር ተመሳሳይ ነው።

ብዙ ችግሮች ከሱዳን ጋር የተፈጠሩ ቢሆንም በመካከል የተፈጠረ የጎላ ችግር አልነበረም። ለምን ቢባል በእነዚህ ጥቅሞች እየተሳሰርን ነው። ከደቡብ ሱዳን ጋር ያለው ግንኙነት እየሰፋ ነው። በመንገድ ሥራ ሁሉ የመሰማራት ፍላጎቶች እየታዩ ናቸው። ያለንን ውስን ሃብት ማካፈል ችለናል። በዚህም እርስ በእርስ መተሳሰር ተችሏል፡፡

ዲፕሎማሲው ቀስ እያለም ቢሆን ሀገርንና ቀጣናውን ሊጠቅም በሚችል መልኩ መስመር እየያዘ መጥቷል። ነገር ግን ከተፅዕኖና ከችግሮች ነፃ ነው ማለት አይደለም፤ ሊሆንም አይችልም። ኢትዮጵያ በተደጋጋሚ ሱዳን ውስጥ ሠላም ለማምጣት የበዛ እንቅስቃሴ አድርጋለች። ነገር ግን ከዚህም ባለፈ ብዙዎች የተለያየ ፍላጎት እያሳዩ ነው። ስለዚህ ሠላም የመምጣት ዕድሉ ይዘገያል እያለች በተደጋጋሚ ሃሳብ አንስታለች። ይሁንና እንደዚህ አይነት ውስብስብ ጉዳዮች ውስጥ ገብታ ተጨማሪ ራስ ምታት ላለመሆን፤ አሁን ላይ እራሷን ወደኋላ እየጎተተች ነው፡፡

ቀጣናው ትኩረት የሚስብ እንደመሆኑ በተለይም ከእሥራኤል ጋዛ ጦርነት፣ ከሀውቲ ጥቃት ጋር በተያያዘ ወደ አፍሪካ ቀንድ የሚደረገው ትኩረት እየሰፋ ነው። በመሆኑም አንድ ሀገር ብቻዋን ምንም ማድረግ የማትችልበት ሁኔታ እየመጣ ነው። በጋራ መሥራት የሚቻሉትን በጋራ በማጥናት መሥራት ይቻላል። አላስፈላጊ ጫና ውስጥ የሚከቱ ነገሮች ከሆኑ ግን እራስን እያገለሉ መጓዝ ነው። እንዲህ አይነት ሁኔታዎችም እየታዩ ናቸው።

በጋራ መሥራት የሚቻልባቸው ነገሮች ላይ አብሮ በማጥናት እና በመሥራት አላስፈላጊ ነገሮች ሲያጋጥሙ ደግሞ ራስን ማግለል ያስፈልጋል። አሁን የኢትዮጵያ መንግሥት ይህንን እያደረገ ነው። ሶማሊያም ሆነ ሱዳን ላይ ተመሳሳይ ችግሮች አሉ። ደቡብ ሱዳን ላይ ከዚህ በፊት ኢትዮጵያ በጣም ስትሠራ ነበር። አሁን ኬንያ ዋና ተዋናይ ሆና እየመጣች ነው። ኬንያ ከተሳካላት መልካም ዕድል ብሎ መተባበር ነው። በበጎ መንፈስ የሚመጡ ተዋንያን ካሉ አብሮ መሥራት ነው። በአጥፊ መንፈስ እኔ ብቻ ላድርግ ብለው የሚመጡ ካሉ እስከሚቻለው ድረስ ሔዶ ራስን ማግለል ነው። እንደዚህ ዓይነት ነገር ቀጣናው ላይ አለ።

**አዲስ ዘመን፡- የባሕር በርን በተመለከተ ኢትዮጵያ እየሄደች ያለችበትን መንገድ እንዴት ያዩታል?**

**ዳርእስከዳር (ዶ/ር)፡-** ኢትዮጵያ የባሕር በር ያስፈልጋታል አያስፈልጋትም፤ ጥያቄው መቅረብ አለበት የለበትም የሚለውን ድልድይ አልፈነዋል። እነዚህ አሁን ተመልሰዋል። ብዙ የዓለም ክፍል ያስፈልጋችኋል። የባሕር በር ጥያቄ መቅረቡም ችግር የለውም የሚባልበት ደረጃ ላይ ተደርሷል። ቀጣዩ ነገር እንዴት ታገኙታላችሁ የሚለው ነው። ለእዚህ ደግሞ ብዙ ፖለቲካዊ እና ሕጋዊ አቅጣጫዎች እየታዩ ናቸው።

የባሕር በር ጥያቄ ለኢትዮጵያ የግድ የሕልውና የሆነ ጉዳይ ነው። ይህንን የምንለው የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ታዳጊ ነው። ታዳጊ ኢኮኖሚ እና ታዳጊ ሕዝብ አለ። ይህንን የሚያህል ሕዝብ ይዞ በትንሽዬ ፖርት ላይ፤ ለዛውም በደካማ መሠረተ ልማት በአንድ የባቡር መስመር፤ እየተበላሸ በሚቋረጥ አንድ የአስፓልት መንገድ ላይ ለዘላለም እኖራለሁ ብሎ የሚያስብ ሀገር የለም።

አንደኛ በጅቡቲ በኩል በቂ መሠረተ ልማት የለም። በሌላ በኩል አንድ ፖርት ላይ መንጠላጠል ደግሞ ለተጋነነ ዋጋ ያጋልጣል። ይኼኛውን ወደብ ከዚህኛው ወደብ አወዳድሬ እጠቀማለሁ የሚባል ነገር የለም። የሚሠራው እንደተፈለገ በባለወደቡ በተወሰነ ሂሳብ ነው። በሌላ በኩል አንድ ሀገር በምንም መልኩ የሌላ ሀገር ጥገኛ መሆን የለበትም። ይህ ከደኅንነትም አንፃር መታየት አለበት።

ደኅንነት ሲባል ከፖለቲካ አንፃር ሳይሆን ከዋስትና አንፃርም መታየት አለበት። ለምሳሌ ድንገት ጅቡቲ ውስጥ ወይም በመስመሩ ላይ የሆነ ነገር ቢፈጠር፤ መርካቶ ላይ የፍጆታ ዋጋ በከፍተኛ ሁኔታ ያሻቅባል። ሌላው የምናስገባቸውን የፀጥታ መሣሪያዎች የሚለውን እንኳን ትተን የፍጆታ ዕቃ ለማግኘት አዳጋች ሊሆን የሚችልበት ሁኔታ ያጋጥማል። ስለዚህ ለኢትዮጵያ አማራጭ በጣም ያስፈልጋታል።

በሌላ በኩል ከደኅንነት አንፃር ለምሳሌ የኢትዮ ኤርትራ ጦርነት ሲጀምር፤ በዛ ጊዜ በአሰብ ወደብም እንጠቀም ነበር። ወዲያውኑ ጦርነቱ ሲጀመር ኤርትራ ውስጥ ወደ ኢትዮጵያ ሊጫኑ ተራግፈው የነበሩ ንብረቶች በሙሉ እዛው ቀሩ። ንብረቱ ይቅር ግድ የለም። ነገር ግን ድንገት ሳንዘጋጅ በጅቡቲ በኩል ለማስገባት ተገደድን። ጅቡቲ ስንጠቀም በሰው ወደብ ስለምንጠቀም የማዕቀብ ሰለባ ሆነናል። ጅቡቲ ላይ ሌላው ቁጭ ብሎ እኛን ይከታተላል። በቀጣይ ምን ይሆናል? ምን ሊፈጠር ይችላል? የሚለውን አናውቅም።

የትግራይን ጦርነትም እንጥቀስ። እዛ ጦርነት ውስጥ መግባታችን አለመታደል ነው። ነገር ግን ጦርነቱ በተለይ ሁለተኛ እና ሦስተኛው ዙር ላይ አቅጣጫው ያተኩር የነበረው መስመሩን በመያዝ፤ በኢትዮጵያ ላይ ትልቅ ችግር ለመፍጠር ታስቦ ነበር። ስለዚህ ሀገራዊ ደኅንነታችን ራሱ አደጋ ውስጥ ይገባል ማለት ነው። ምናልባት ደግሞ ሌላ ልናየው የምንችለው ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለምክር ቤት አባላት አጀንዳ አድርገው ሲናገሩ፤ ኢትዮጵያ በአፍሪካ ተፅዕኖ ፈጣሪ ለመሆኑ የሚቀራት አንድ ነገር ብቻ ነው። እርሱም በቅርቡ ይሳካል ብለው ስለባሕር በር ሲናገሩ ነበር።

ወደ ፊት ኢትዮጵያ በምሥራቅ አፍሪካ ወይም በአፍሪካ ደረጃ ተፅዕኖ ፈጣሪ መሆን ትችላለች ወይ? ሲባል የመሆን ዕድል አላት አቅሙ አላት፤ ነገር ግን አሁን ባለው ሁኔታ ተፅዕኖ ፈጣሪ መሆን አትችልም። ስለዚህ ያለንን አቅም ለመጠቀም የባሕር ኃይል በማቋቋም የወታደር ኃይሉን በመሬት እና በአየር ላይ ብቻ ሳይሆን በውሃ ላይም መኖር አለበት። ለዛ ደግሞ የባሕር ኃይል እናቋቁማለን ተብሎ ከለውጡ ጀምሮ ሲሠራ ነበር። እነዛን መሬት ላይ እናስቀምጣቸውም፤ የውሃ አካል ያስፈልጋቸዋል።

እንደተራ ዜጋ ደግሞ ከተቻለ አሰብን ካልሆነም ሌላ የባሕር በር ብናገኝ ብዬ አስባለሁ። ኢሕአዴግ ከፍተኛ ድጋፍ ያጣበት ትልቅ ምክንያት ይኸው ነው። የባሕር በር ቢገኝ መንግሥት ከፍተኛ ድጋፍ ያገኛል።

በተጨማሪ በተለያየ ምክንያት የባሕር በር ያስፈልጋል። ከታሪክ አንፃር እናንሳም ቢባል አሰብ፣ ታጁራ፣ በርበራ፣ ዘይላ እነዚህ ሁሉም አካባቢዎች የኢትዮጵያ የባሕር መዳረሻ ነበሩ። ነገር ግን ኦቶማንስ ከመጡ በኋላ አንዴ አንዱን ስናጣ፤ ሌላ ጊዜ ደግሞ ሌላኛውን ስናጣ፤ ከ16ኛው ክፍለ ዘመን በኋላ አንዴ ወደ ዘይላ እያልን ቆየን። ከዛ ኮሎኒያሊዝም ሲመጣ ያው የሚታወቀው ሆነ። አንዴ የእኛ የነበረን ነገር መጠየቅም ላያስፈልግ ይችላል። ያው በፊት ስለነበረን አሁንም ይኑረን ሲባል ለጎረቤት ሀገራትን ሊያስቆጣ ይችላል። ነገር ግን ይሄን ጥያቄ የጎረቤት ሀገሮች ችላ ይሉታል ብዬ አላስብም።

ቀንዱ ላይ ያለችው ትልቋ ሀገር፤ በር ተዘግቶባት በሌሎች ሀገሮች እስከ መቼ ጥገኛ መሆን እንደሚቻል አይታወቅም። ከኤርትራ ጋር የተፈጠሩ አንዳንድ ሁኔታዎች፤ በኢትዮ ኤርትራ ጦርነትም ልናገኝ እየቻልን እንዳጣን ፖለቲካው ያሳየናል። ስለዚህ ይህንን ጉዳይ ማንሳት ወቅታዊ ብቻ ሳይሆን እጅግ አስፈላጊ ነው። አሁን ዋናው ነገር በምን መንገድ እናግኘው የሚለው ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያ የባሕር በር ልታገኝባቸው የምትችልባቸውን አማራጮች እንዴት ያዩታል?**

**ዳርእስከዳር (ዶ/ር)፡-** ሕጉ በቀጥታ የባሕር በር ማግኘት ይቻላል አይልም። ነገር ግን መውጫ መግቢያ የማግኘት መብት እንዳለን ያስቀምጣል። ይኼም ከዛ ሀገር ጋር በሚኖራቸው መልካም ስምምነት መጠቀም ይችላሉ ይላል። መግቢያ መውጫ የማግኘት ጉዳይ ጅቡቲ ብቻ ሳትሆን ሶማሌ ላንድም ፈቅዳልናለች። ግን ደግሞ ሕጉ ላይ ያለው በሁለቱ ሀገራት መካከል መደራደር ከተቻለ ባሕር በር ማግኘት እንደሚቻል ተቀምጧል። ለምሳሌ ጅቡቲ የሆነች መሬት በሆነ ዓይነት መንገድ ብትሰጠን፤ ኢትዮጵያ በአንድ ጊዜ የባሕር በር ባለቤት ሆነች ማለት ነው።

ለሕግ መገዛት ጥሩ ስለ ሆነ እና ኢትዮጵያም የሠላም አማራጭን የምትከተል ሀገር ስለሆነች እየሄደች ያለችውም ሠላማዊ በሆነ መንገድ ነው። ዋናው ትኩረት ማድረግ ያለብን ፖለቲካውን ነው። ፖለቲካው ላይ ያሉትን ዕድሎች በደንብ ማጤን ያስፈልጋል። ያሉ ጥያቄዎች ምንድን ናቸው? ለማን ምን መስጠት አለብን? ከማን ምን መቀበል አለብን? የሚለውን በደንብ አስልቶ መሥራት ነው። የተገኘውን አማራጭ ሁሉ መጠቀም ያስፈልጋል። አሁን የመግባቢያ ስምምነቱም የእዛው አካል ነው።

ሶማሌላንድ ላለፉት 31 ዓመታት ከሶማሊያ የተገነጠለችው በኢትዮጵያ ምክንያት አይደለም። በራሷ ምክንያት ነው። የሶማሊያ ችግር እና የሶማሌላንድ ችግር የእኛ ችግር አይደለም። እኛ ሀገር እየፈጠርን አይደለም። ቀድሞም ሀገር ተፈጥሯል። ኤርትራ ቢባል በኢትዮጵያ መንግሥት እና በትግራይ ተዋጊዎች መካከል በተፈጠረ ጦርነት ኢትዮጵያ ዕውቅና ሰጥታ የተፈጠረች ሀገር ናት ማለት ይቻላል።

ሶማሌላንዶችን ግን ዚያድባሬ በጦር ጀት ጨፈጨፋቸው፤ ከዛም ከዚህ በኋላ የሶማሊያ አካል አንሆንም ብለው የራሳቸውን መንግሥት መሠረቱ። የራሳቸውን የተሻለ ሥርዓት እና መንግሥት መሥርተዋል። ላለፉት 30 ዓመታት ነክተናቸው አናውቅም። ፖለቲካዊ ንግግር ሲደረግ እዛ ጋር ተደረሰ። ደግሞም ሶማሊያዎች ራሳቸው በሕገመንግሥታቸው ሶማሌላንድ የሶማሊያ ግዛት እንዳልሆነች አስቀምጠዋል። ስለዚህ ባለው ነገር እኛ ልንጠቀም ብናስብ ምንም ክፋት የለውም። ክፍተት ካለ ማንኛውንም አማራጭ ከመጠቀም ወደ ኋላ አንልም።

አብሮ የሚሠራ ካለ አብረን እንሠራለን። ይህ ሁሉም ሀገር የሚያደርገው ነው። ለምሳሌ እኛ በዚህ ሰዓት ይህንን አስልተን አብሮን ከሚሠራው ጋር እንተባበራለን። የእኛ ሐቅ ይህ ነው። ግን ደግሞ በጎን የሚጠበቅም የማይጠበቅም ውጤት እያየን ነው። መቼም ሁሉም ነገሮችን ከራሱ ጥቅም አንፃር ነው። ይሄ ጥያቄ የጎረቤት ሀገራትም መካከል በተለይ በአንዳንዶቹ ያልተገራ የመንግሥት ባሕሪ ያላቸው ላይ አላስፈላጊ ምላሽ ሊመጣ እንደሚችል ይታወቃል።

አንዳንዶቹ ደግሞ ነገሩን በጣም በመለጠጥ ከቀጣናው ውጪ ያሉ ሀገሮች ወደ ቀጣናው እንዲመጡ እያደረጉ ነው። አንድ ዓመት ሳይሞላ ብዙ ነገሮች እየተለወጡ እያየን ነው። ለምሳሌ ኤርትራ ምክንያቷን ግልፅ ሳታደርግ ለምን ከሶማሌላንድ ጋር ተፈራረማችሁ ተደራደራችሁ ብላ እየተቃወመች አይተናታል። የት ድረስ ልትሔድ እንደምትችል አይታወቅም፤ መገመት ግን ይቻላል። ስለዚህ የባሕር በር ጥያቄ ቀጣናውንም ሊቀይር የሚችል ትልቅ ጥያቄ ነው። በዚህም በዚያም የተለያዩ አሰላለፎችን ሊስብ እንደሚችል ይታወቃል። በቀላሉ ሊገኝ እንደማይችል ይታወቃል። ብዙ ጥረት እና ልፋት እንዲሁም ብዙ ዋጋ መክፈል ሊጠይቅ ይችላል። ያንን ለማግኘት ብዙ መስጠትም ሊኖርብን ይችላል።

**አዲስ ዘመን፡- ከሶማሊያ ጋር ያለንን ግንኙነት በተመለከተስ ምን ይላሉ?**

**ዳርእስከዳር (ዶ/ር)፡-** ሶማሊያ ላይ የተፈጠረው ምንድን ነው? የሚለውን እንይ ከተባለ የኢትዮጵያ መንግሥት ከ1998 ዓ.ም ጀምሮ፤ ሶማሊያ ውስጥ ሠላም ለማምጣት በሁለትዮሽ ስምምነትም፣ በተባበሩት መንግሥታትም ሆነ በአፍሪካ ኅብረት በኩል አብሮ እየሠራ ነው። 98 ላይ እስላማዊ ኅብረት ፍርድ ቤቶች ተፈጠረ። ሠላማዊ ወታደራዊ ቡድን ተመሠረተና መቋዲሾን እና አካባቢውን እስከ ባዲዋ መቆጣጠር ጀመረ። ከዛ ቀጥሎ «ኢትዮጵያን እወራለሁ አንዋር መስኪድ እሰግዳለሁ ማለት ጀመረ፡፡» በሠላም ሃይማኖታዊ መሠረት አለኝ ብሎ ለመስገድ ቢመጣ ማንም አይከለክለውም ነበር። ነገር ግን ዓላማው መሬቱን ወርሬ የግሌ አደርጋለሁ የሚል ሆነ፡፡

ኢትዮጵያ ላይ ብቻ ሳይሆን በዓለም ደረጃ እንደዚህ ዓይነት የአሸባሪ ኃይል ጉልበት ሲፈረጥም በተለይ ከ1994 ዓ.ም ወዲህ ማለትም አሜሪካን ላይ የናይን ኢለቨን የሽብር ጥቃት ከደረሰ ወዲህ ዓለም ሽብርተኛን የማትታገስበት ዘመን ነበር። ስለዚህ ከ1998 ዓ.ም በኋላ አልሸባብ እየተጠናከረ የተለያዩ አካባቢዎችን ሲይዝ፤ ከዛ ኢትዮጵያ እመጣለሁ ሲል፤ የኢትዮጵያን ጥቅም የሚነካ ነበር። የኢትዮጵያን ብቻ ሳይሆን በቀጣናው ላይ ትልቅ ሚና ያላትን የአሜሪካንንም ጥቅም የሚነካ ነበር። ስለዚህ ኢትዮጵያ ከሌሎች ኃያላን ሀገራት ጋር ምላሽ መስጠት ነበረባት፤ ስለዚህ ገባች። ከዛ ጊዜ ጀምሮ ሶማሊያ ውስጥ ሽግግር መንግሥት በመመሥረት፤ ሶማሊያን በመጠበቅ ብዙ ጥረት ሲደረግ ነበር።

አሁን ሶማሊያ ለደረሰችበት ስኬት ኢትዮጵያ ብዙ ዋጋ ከፍላለች። ከዛ ከኢትዮጵያ ጣልቃ መግባት በኋላ፤ በአፍሪካ ኅብረት ውሳኔ መሠረት ዩጋንዳ፣ ኬንያ እና ሌሎች ሀገራትም እንዲገቡ ተደረገ።

ኢትዮጵያ ከውጪ ያለውን ሠራዊቷን ሙሉ ለሙሉ ብታስወጣ መቋዲሾስ መቀጠል ትችላለች ወይ? ኢትዮጵያ ብትወጣ፣ ኬንያውያን፣ ታንዛኒያውያን ሊተኳት ይችላሉ? የሚለው ያጠያይቃል። እኛ ሠላም አስጠብቁ ካሉን ከማስጠበቅ ወደ ኋላ አንልም። የኢትዮጵያ መውጣት ሶማሊያን ምን ሊያደርግ እንደሚችል ይታወቃል። የኢትዮጵያ አለመግባት አልሸባብን ሊያጠነክረው ይችላል። ስለዚህ ኢትዮጵያ ልትገባ ትችላለች ወይም ሌሎች አማራጮች ሊኖሩ ይችላሉ። በቀጣይ ሁሉንም የምናየው ይሆናል።

**አዲስ ዘመን፡- ስለነበረን ቆይታ በዝግጅት ክፍሉ ስም እጅግ አመሠግናለሁ።**

**ዶ/ር ዳርእስከዳር፡-** እኔም አመሠግናለሁ።

ማህበራዊ

# አስኳላ





ፎቶ፡- በገባቦ ገብሬ

የገላን ጉራን አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውጫዊ ከፊል ገጽታ፤

# ደስታን የፈጠረ ትምህርት ቤት

**ጽጌረዳ ጫንያለው**

የትምህርት ጥራትን በማረጋገጥ የትምህርት ቤቶች ውስጣዊ አደረጃጀት ከፍተኛ አስተዋፅዖ ይኖራቸዋል። የተማሪዎችን ባሕርይ እና የመማር ማስተማር ሁኔታን በማሻሻል በኩል የማይተካ ሚና አላቸው። ተማሪዎችን በእውቀት፣ በክህሎት፣ በአመለካከት ብቁ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል። ከዚህም አንጻር እንደ ሀገር በተለያየ መልኩ የተለያዩ ትምህርት ቤቶች እየተገነቡ ይገኛሉ። በገላን ጉራ መንደር ውስጥ ለልማት ተነሺዎች ተብሎ የተገነባው የገላን ጉራ ትምህርት ቤት ደግሞ ለዚህ እንደ ጥሩ ማሳያ ተደርጎ የሚወሰድ ነው። ትምህርት ቤቱ ከካዛንችስ፣ ከፒያሳ፤ ከመገናኛ ከሸሮሜዳ አካባቢ የመጡ ተማሪዎች የሚማሩበት ሲሆን፤ ለአካባቢው ነዋሪዎችም መልካም የመቀራረቢያ አጋጣሚን የፈጠረ ነው።

ከቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቱ ጀምሮ መሟላት ያለባቸውን ሁሉ በማሟላትም የተሠራም ነው። ለአብነት የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቱን ብናነሳ ሕጻናቱ የሚተኙበት፤ የሚመገቡበትና የሚማሩበት እንዲሁም የሚፀዳዱበት ደረጃውን የጠበቁ ክፍሎች ተገንብተዋል። መፀዳጃ ክፍሎቹም በፆታቸው እንዲመች ተደርጎ የተገነቡ ናቸው። ከዚያም ባሻገር ሕጻናቱ ወጣ ሲሉ የሚዝናኑባቸው ቦታዎች ተመቻችተውላቸዋል።

ወደ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቱ ስንገባም ይህንኑ ሁኔታ እንመለከታለን። ትምህርት ቤቱ ከአዲስነቱ የተነሳ ነገሮች ያልተስተካከሉለት ቢመስሉም አብዛኛው ሥራው የሚስብና ከትምህርት ቤቱ ውጡ የማያሰኝ ነው። እንደ ሀገር በትምህርት ቤት ውስጥ የተማሪዎች መማርና የመማር ውጤቶች በጎ ተፅዕኖ የሚያሳድሩት የትምህርት ቤት ዓበይት ርዕሰ ጉዳዮችንም አሟልቶ የተገኘ ነው። እነዚህም መማርና ማስተማር፤ የትምህርት ቤት አመራር፤ ምቹ የኅብረተሰብ ተሳትፎና የትምህርት ሁኔታና አካባቢ የሚሉት ሲሆኑ፤ ትምህርት ቤቱ እነዚህን ሁሉ ነገሮች አሟልቶ አግኝተነዋል።

ግቢው በአረንጓዴ ችግኞች ያማረ ባይሆንም አቧራ እንዳያስቸግር በማሰብ በአርቴፊሻል ሣሮች ተውቧል። ተማሪዎች ዘና ብለው እንዲማሩም ልዩ ልዩ የመዝናኛ ቦታዎች ተገንብተዋል። አንዱ ሰፊው ስታዲየም ነው። ሌላው በትንሽ ስፍራ ላይ ያለችው የኳስ ሜዳና የቅርጫት ኳስ መጫዎቻ ሜዳው ነው። ይህ ደግሞ ተማሪዎች በዙሪያው ተቀምጠው እንዲያጠኑ፤ አለያም ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎችን እንዲያደርጉ፤ ካሻቸው ደግሞ በቡድን ሆነው እንዲመካከሩ ዕድል ይሰጣቸዋል። ክፍላቸውም ያማረ በመሆኑ በዚያ የፈለጋቸውን እንዲያደርጉ የሚያስችላቸው ነው። ለዚህም ምስክርነታቸውን የሚሰጡን አሉ።

አንዱ ተማሪ ኢምራን መሐመድ ነው። ስለ ትምህርት ቤቱ ሲናገር፤ ይህ ልዩ ምድር ለእኛ ገጸ በረከት ነው። ከዚህ በፊት በነበርንባቸው ትምህርት ቤቶች ያላየነውን ነው የሰጠን። የትምህርት ቤቱ ፅዳትና አሠራርም ለእኛ ከነበርንበት ስፍራ በእጅጉ የተሻለ ነው። በተለይም የትምህርት ክፍሎቹና የስፖርት ሜዳው ወይም ስታዲየሙ እጅጉን ደስታን የፈጠረልን ነው። ምክንያቱም ትምህርት ቤት መማሪያ ብቻ ሳይሆን ማጥኛም፤ መዝናኛም፤ ራስንም ማዳመጫ ነው። እናም ገላን ጉራ ትምህርት ቤት ይህንን ሰጥቶናል።

ተማሪ ኢምራን አሁን ያለበት ትምህርት ቤት በእጅጉ ተመችቶታል። ትምህርት ቤቱ መኖሪያ ቤቱ እስኪመስለው ጭምር እየቆየበት ነው፤ ያጠናበታልም። በተለይም ከስታዲየሙ ግንባታ ጋር ተያይዞ ብዙ ደስ የሚሉ ተግባራትን እያከናወነ ይገኛል። ዘና ከማለት አልፎም ከጓደኞቹ ጋር ንጹሕ አየር እየሳቡ በቡድን የሚያጠኑበትን ዕድል ፈጥሮላቸዋል። በዚህም ትምህርት ቤቱን የሚስብና አትራቂ የሚያሰኝ ሆኖ አግኝተነዋል ይላል።

ተማሪ ኢምራን የዘጠነኛ ክፍል ተማሪ ሲሆን፤ ከካዛንችስ ምሥራቅ ጎሕ ትምህርት ቤት ከመጡት ተማሪዎች መካከል ነው። ነባር ትምህርት ቤቱ አሁን ከአለበት ጋር ሲያነጻጽረው በብዙ መልኩ የተለየ እንደሆነ ይናገራል። የቀድሞ ትምህርት ቤቱ የመዝናኛ ቦታውና ስፋቱ ምንም ዘና የሚያደርግ አይደለም። ስታዲየም ይቅርና ጥሩ የመጫወቻ ሜዳ እንኳን የለውም። ስፖርት ሲሠሩም ሁልጊዜ ልብሳቸው፤ ሰውነታቸው በአቧራ ይሸፈናል። አሁን ግን ይህ አያጋጥማቸውም። ስታዲየሙ በአርቴፊሻል ሳር የተሸፈነ በመሆኑ ምንም አይነት አቧራ አያገኛቸውም። ጎን ለጎን የቅርጫት ኳስ መጫወቻ የተመቻቸላቸው በመሆኑ ተማሪው በፈለገው ዘርፍ ዘና እያለ ትምህርቱን ይከታተላል።

ተማሪ ኢምራን በምሥራቅ ጎሕ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ብዙ ነገር ይጎል ነበር። ትምህርት ቤት ውስጥ የሚያቆየው የመምህራን የማስተማርና እነርሱን የመደገፍ ሁኔታ ብቻ ነው። አሁን ግን ብዙ ነገሮች እርሱን ማርከውታል። አንዱ የትምህርት ቤቱ ምቹነት ሲሆን፤ ሌላው መምህራን በትምህርታቸው ወደ ኋላ እንዳይቀሩ የሚያደርጉት ጥረት ነው። ይሁን እንጂ በአፋጣኝ እንዲሟሉላቸው የሚፈልጋቸው ነገሮች እንዳሉ ሳይጠቁም አላለፈም። እነዚህም ትምህርት ቤቱ አዲስ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ያሉ ችግሮች ናቸው። ቤተ መጽሐፍቱ በሚገባ አልተደራጀም፤ ቤተ ሙከራም የለም። እናም በተለያየ መንገድ መምህራን እያገዙን ቢሆንም ትምህርት ቤቱ በአፋጣኝ መፍትሔ የሚሰጥበትን መንገድ ቢያመቻች ሲል አስተያየቱን ለግሷል።

ተማሪ ሀያት ዋሲሁን ሌላኛዋ ምስክርነቷን የሰጠችን ነች። እንደ ኢማን ሁሉ በትምህርት ቤቱ ምቹነት መደሰቷን ትገልጻለች። ይህ ትምህርት ቤት በተለይም ለሴቶች ጥሩ ዕድልን ይዞ የመጣ እንደሆነ ታስረዳለች። ምክንያቱም ከቤታቸው ርቀው እንዳይሄዱ ያግዛቸዋል። በትምህርት ቤቱ ውስጥ እያጠኑና የቤት ሥራዎችን እየሠሩ ቢቆዩም ለቤታቸው በቅርብ ርቀት ላይ የተሠራ በመሆኑ የሚያስጨንቃቸው ነገር የለም። እስካሁን ካለችበት ሁኔታ አንጻር በአሁኑ በእጅጉ መደሰቷን ትናገራለች።

ቀደም ሲል በምትማርበት ትምህርት ቤት መምህሮቿ የተሻሉ እንደሆኑ አንስታ፤ ለማጥናት ያለው ምቹነት ግን እምብዛም እንደሆነ ትጠቅሳለች። ይህ ትምህርት ቤት ግን ፀጥታና ምቹነት የተሻለ ተማሪ እንድትሆን እንደሚያግዛትም ታምናለች። ለዚህም መምህሮቻቸው እያገዟቸው እንደሚገኙም ታስረዳለች። የእነርሱን ልዩ ድጋፍም ሳታደንቅ አላለፈችም። ትምህርት ሲጀምሩ ጀምሮ አቅማቸውን እየለዩ ለእነርሱ የሚመጥን ትምህርት እየሰጧቸው እንደሆነም ታነሳለች። በአቅራቢያቸው ካሉ ትምህርት ቤቶች ጋር ጭምር በመነጋገር የተለያዩ መጽሐፍትን የሚያገኙበትን ሁኔታ እንዳመቻቹላቸው ጠቅሳ ለዚህም ምስጋና አቅርባለች።

ሀያት እንደ ኢማን ሁሉ ቢሟሉልን የበለጠ ውጤታማ እንሆናለን የምትላቸው መሠረተ ልማቶችና ግብዓቶች አሉ። አንዱ የአይሲቲ ክፍል ነው። ሌላው ደግሞ ቤተ መጽሐፍት ሲሆን፤ በመምህሮቻችን በቅርቡ ይህ ነገር እንደሚሟላልን ተነግሮናል። ነገር ግን ውጤቱ ቶሎ መታየት አለበትና ሁሉም ተረባርቦ ለመፍትሔው መሥራት ይገባልም ስትል ሀሳቧን ገልጻለች።

አቶ አስቻለው ኃይሉ የገላን ጉራ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ የትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር ናቸው። ከደራርቱ ቱሉ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ትምህርት ቤቱን ለመምራት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ በተሰጣቸው ኃላፊነት መሠረት ተዛውረው መምጣታቸውን ይናገራሉ። አሁን ትምህርት ቤቱን የመምራት ትልቅ ኃላፊነት እንደተጣለባቸው ያስባሉ። ከዚህ አንጻርም ትምህርቱን ሲያስጀምሩ በተለየ ወኔ እንደሆነ ያነሳሉ።

የተረከቡት ትምህርት ቤት ብዙዎች የተደመሙበት ነው። ለዘጠና ቀን ታቅዶ በስልሳ ቀን የተጠናቀቀ እንደሆነም አውቀዋል። እናም ይህንን እውነት በተማሪዎችም ውጤት መድገም ይፈልጋሉ። በመሆኑም በመንግሥት በጀት ብቻ ይህንን ማድረግ አይችሉምና የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን እያደረጉ ይገኛሉ። አንዱ ተማሪዎች ማንበቢያ ክፍል ብቻ ሳይሆን የሚያነቡት መጽሐፍም ያስፈልጋቸዋል በማለት «ሁለት ያለው አንድ ይስጥ» የሚል እንቅስቃሴ ጀምረው መጽሐፍትን እየሰበሰቡ ናቸው። በተገኙት መጽሐፍትም ቤተ መጽሐፍቱ አገልግሎት እንዲሰጥ ሥራ ጀምረዋል። ሌላው «ሁለት ያለው አንድ ይስጥ» እንቅስቃሴያቸውን በኮምፒውተሮች ዙሪያም አድርገዋል። በዚህም ወደ አስር ኮምፒውተሮችን አግኝተው አገልግሎት መስጠት ጀምረዋል።

«ተማሪዎች ብቻቸውን የሚንቀሳቀሱ አይደሉም። በሁሉም ዘርፍ ውድድር ይጠብቃቸዋል። ያለው ችግር ከሌሎቹ ጋር እንዳይወዳደሩ ሊያደርጋቸው አይገባም» የሚሉት ርዕሰ መምህሩ፤ ሁሉም ጋር ተወዳድረው አሸናፊ፤ የተሻለ ውጤት የሚያስመዘግቡ እንዲሆኑ ለማስቻል ልዩ ልዩ ጥረቶች እየተደረጉ እንደሆነም ያነሳሉ። በአብነት የሚጠቅሱትም በትምህርታቸው ወደ ኋላ እንዳይቀሩ ቅዳሜና እሁድ ሳይባል አስጠኚ መምህራንን በመመልመል በልዩ ትኩረት እንዲማሩ ማስቻሉን ነው። በተመሳሳይ በአካባቢያቸው ያሉትን ፀጋዎች በመጠቀም የተማሪዎችን ውጤታማነት ማሻሻል ነው። ለምሳሌ ዩኒቨርሲቲ ጭምር በአካባቢው ላይ ስላለ የተደራጁ ቤተ መጽሐፍትንና ቤተ ሙከራዎችን እንዲጠቀሙ ለማስቻል የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን በማድረግ ላይ መሆናቸውን ይናገራሉ።

የግቢ ማማር የመጨረሻ ግብ እንዳልሆነ የሚጠቁሙት አቶ አስቻለው፤ ከግቢ ውበት ባሻገር ተማሪዎች ላይ መሠራት ያለበት መሠረታዊ ነገር አለ። ይህም የተማሪዎችን ውጤት ማሻሻልና ውጤታማ ተማሪ መፍጠር ነው። ለዚህ ደግሞ በሥነምግባር የታነጸ ዜጋ ያስፈልጋል። ይህንን ለማድረግ ደግሞ ትምህርት ቤቱ ምቹነት አለው። አዲስ መምህር፤ ርዕሰ መምህርና አዲስ ተማሪን ይዞ የተነሳ ነው። በመሆኑም ተማሪዎች በትምህርት ቤቱ ከእውቀት ባሻገር የሚታዩ መሆን መቻል አለባቸው። በትምህርት ቤቱ መልካም ባሕልን የሚያጎለብቱ፤ ሕግን የሚያከብሩ፤ ተጠያቂነትን የሚያሰፍኑና አዲስ መሰባሰብ የተቃኙ መሆን ይጠበቅባቸዋል። ሁሉም አዲስ ባሕልን፤ ልምድንና እውቀትን አስተባብሮ የሚይዝበት ሊሆን ይገባል። እናም ይህንን መሠረት ለመጣል ሁሉም እየተጋ ይገኛልም ብለውናል።

የገላን ጉራ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የትምህርት እርካታን የሚሰጥ መሆን አለበት። ተግባሩ ደግሞ ከተማሪዎች ይነሳል። ከዚያ ወላጆች ጋር ይደርሳል የሚሉት ርዕሰ መምህሩ፤ አሁን በአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቱ 157 የሚደርስ ተማሪ እንዳለ ይናገራሉ። ገና በመምጣት ላይ ያሉ ተማሪዎች በመኖራቸውም ቁጥራቸው ከዚህም እንደሚልቅ ያስረዳሉ።

ይህ ትምህርት ቤት ለልማት ተነሺዎች ብቻ ሳይሆን ለአካባቢው ማኅበረሰብም የተበረከተ ልዩ ስጦታ እንደሆነ የሚናገሩት አቶ አስቻለው፤ ትምህርት ቤቱ በቅርብ ርቀት ላይ ለሚገኙ ተማሪዎችና ወላጆች እፎይታን የፈጠረ እንደሆነ ያስረዳሉ። የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በአካባቢው ላይ በስፋት ቢኖርም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ግን እንደ ልብ አይገኝም። በዚህም ተማሪዎች ርቀው እንዲሄዱ ይገደዳሉ። ቤተሰብም ልጆቹ በሠላም ለመግባቱ ይጨነቃሉ። አሁን ግን ይህ ሁኔታ መፍትሔ በማግኘቱ ብዙዎች ደስተኞች ስለመሆናቸውም ይናገራሉ።

መምህር ኃይሌ ተዝገራ ከአቃቂ ቃሊቲ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የመጡና አሁን በገላን ጉራ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሒሳብ መምህር በመሆን የሚያገለግሉ ናቸው። ተማሪዎቻችን የእኛ ኃላፊነት ናቸውና የትምህርት ቤቱ መሠረተ ልማትና ግብዓት እስኪሟላ ድረስ እነርሱን ለመደገፍ የማናደርገው ነገር አይኖርም ይላሉ። አሁን ላይ አማራጭ የሚሏቸውን ተግባራት እያከናወኑ እንደሆነም ይገልጻሉ። አንዱ ከዚህ ቀደም ያስተምሩባቸው የነበሩ ሞዴሎችን ይዘው በመምጣት ትምህርቱን በሚገባቸው መልኩ መስጠት እንደሆነም ይናገራሉ።

ተማሪዎቹ አዲስ ከመሆናቸው የተነሳም አቅማቸውን የመለየት ሥራ ሁሉም መምህር በየትምህርት አይነቱ እያከናወነ እንደሚገኝ የጠቆሙት መምህሩ፤ አንዳንድ የትምህርት አይነቶች የግድ ቤተ ሙከራ የሚፈልጉ በመሆናቸው የሚደርሱበት ምዕራፍ ላይ ቆም ብለው በቻሉት ልክ በታብሌት እንዲሁም በሞባይላቸው የተግባር ትምህርቱን እንዲሠሩ እየተደረገ እንደሆነ ያነሳሉ። አክለውም ጊዜው የቴክኖሎጂ በመሆኑ አብዛኛውን ትምህርት ተማሪዎች ጭነው እንዲመጡ በማድረግ የመማር ማስተማር ሥርዓቱን ለማሳለጥ እየተሞከረም እንደሆነ ይናገራሉ።

ከቂሊንጦ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ጋር በመወያየት ተማሪዎቻቸው በቁጥራቸው ብዙ ስላልሆኑ ቤተ መጽሐፍትና ቤተ ሙከራዎችን እንዲጠቀሙ መደላደልን መፍጠራቸውንም ያስረዳሉ። ይህ በእንዲህ እንዳለም የግብዓትና ልማቱ ጉዳይ በአጭር ጊዜ እንደሚፈታ ያምናሉ። ለዚህም ሁሉም የትምህርት ቤቱ ማኅበረሰብ ርብርብ እያደረገ እንደሆነም ይጠቅሳሉ።

ስፖርት እና መዝናኛ

# ፋሽን

## ከኦሮሞ የባሕል አልባሳት መዘመን ጀርባ ያለችው ዲዛይነር

**ቤዛ እሸቱ**

በዓልን ከዶሮና ጠላ፣ ከቄጤማው ጉዝጓዝና ከምግብ መጠጡ እኩል በዓል የሚያስመስሉት የባሕል አልባሳቶች ናቸው። በበዓላት ወቅት በገጠርም ይሁን በከተማ በባሕል አልባሳት አጊጦና ተውቦ መታየት የተለመደ የሆነውም ለዚህ ነው።

ከበዓላት ወቅት ውጪ የባሕል አልባሳት በብዙዎች ዘንድ ሲዘወተር አይታይም። የባሕል አልባሳት ከበዓል ወቅት ውጪ የባሕል ዘፈን ክሊፖች፣ የሃይማኖት ቦታዎችና የሠርግ ዝግጅቶች ላይ ብቻ የተገደቡ ናቸው ማለት ይቻላል።

የኦሮሞ የባሕል አልባሳት ደግሞ በተለይ በኢሬቻ በዓል ላይ በስፋት ይታያሉ። ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ግን በኦሮሞ የባሕል አልባሳት ከኢሬቻ በዓል ውጪ እየተዘወተሩ ማየት እየተለመደ መጥቷል። ለዚህም አልባሳቱ አይነግቡ ሆነው በሚያማምር ዲዛይን መሠራት መጀመራቸው አንዱ ምክንያት ሊሆን ይችላል።

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በኦሮሞ ባሕላዊ አልባሳት መዘመንና ማማር ዲዛይነሮች ትልቅ አብዮት መፍጠራቸውን ብዙዎች ይስማማሉ። ይህን አብዮት ከፊት ከሚመሩት መካከል የሎቲ ዲዛይን ባለቤት የሆነችው ዲዛይነር መርሲሞይ ኩምሳ (ሜርሲ) አንዷ ነች።

ሜርሲ ትውልዷ አዲስ አበባ ነው። ቤተሰቦቿ ስለ ባሕል እንድታውቅ አድርገው አሳድገዋታል። የኦሮሞ የባሕል አልባሳትን እየለበሰችም አድጋለች። ከበዓላት ባሻገር በትምህርት ቤት ቆይታዋ የብሔር ብሔረሰቦች ቀንና መሰል አከባበሮች ላይ በነዚህ የባሕል አልባሳት አጊጣለች። ይህም በዓይነት የተለያየ የሆነውን የኦሮሞ የባሕል አልባሳትን አንዱን ከአንዱ እንድትለይ አድርጓታል።



ሜርሲ በኢሬቻ በዓል ላይ ስትታደም በርካቶች በተለያዩ የኦሮሞ የባሕል አልባሳት ተውበው አይታ ተገርማለች። ይህም ለራሷም ይሁን ለሌሎች የኦሮሞን የባሕል አልባሳት ይበልጥ አሳምራና ለመሥራት እንድታስብ አድርጓታል። ያምራሉ ብላ ከምታስባቸው ዲዛይኖች ውስጥ እንከኖችን ነቅሳ በማውጣት እንዲህ ቢሆን የተሻለ ነው እያለችም ታስብ ነበር። ሜርሲ ስድስት እህትና አንድ ወንድም አላት። ከፍ እያሉ ሲመጡ ከእህቶቿ ጋር የተሻለ የኦሮሞ የባሕል ልብስ መፈለግ ጀመሩ። ያኔ ታዲያ ገበያ ላይ ያሉት የልባቸውን መሻት አልሞላ ቢሏቸው ከኢንተርኔት ላይ የተሻሉ ዲዛይኖች በመምረጥ እንደሚፈልጉት የባሕል ልብስ ማሠራት ጀመሩ።

በተለይም ዲዛይን ጎበዝ ናት የምትላት ታናሽ እህቷን ንድፎችን በመያዝ ዲዛይነሮችና ልብስ ሰፊዎች ጋር እያሠሩ የልባቸውን መሻት ይለብሱ እንደነበር ታስታውሳለች።

የኦሮሞ የባሕል አልባሳት አልተሠራባቸውም ብላ ማሰብ የጀመረችው ዲዛይነር ሜርሲ፣ አልባሳቱ ይጎድላቸዋል ብላ የምታስባቸውን ክፍተቶች ለማስተካከል ከሰው ከመጠበቅ የራሷን አሻራ ለማሳረፍ ቆርጣ እንድትነሳ አድርጓታል። ካላት ፍላጎት በተጨማሪ በእውቀት ብትደግፈው የተሻለ እንደሚሆን ስላመነችም የዲዛይን ትምህርት ቤት ገብታ ትምህርት ቀሰመች። ከዚያም ለተወሰነ ጊዜ በቤት ውስጥ ትዕዛዞችን እየተቀበለች መሥራት ጀመረች። በሂደትም “ሎቲ ፋሽን” ስትል የሰየመችውን የባሕል አልባሳት ቤት ከፍታ መንቀሳቀስ ጀመረች። በዚህም የባሕል አልባሳቱ ሳቢ እንዲሆኑ የበኩሏን እያበረከተች ትገኛለች።

ሜርሲ በተለይም የባሕል አልባሳቱ በተለያዩ ዝግጅቶች ከመለበስ በተጨማሪ በአዘቦት ቀን እንዲለበሱ ትኩረት አድርጋ እየሠራች የምትገኘው ሜርሲ፣ በአሁኑ ወቅት የኦሮሞ የባሕል አልባሳት በኢሬቻ በዓል ላይ ብቻ ከመለበስ መሻገራቸውን ትናገራለች። እንደ እሷ ገለፃ፣ ሰዎች ሠርግ፣ ልደት፣ ክርስትና እና የተለያዩ ዝግጅቶች ላይ በዘመናዊ መልኩ በተሠሩት የባሕል አልባሳት ሲያጌጡ መመልከት የተለመደ ሆኗል። አሁን ደግሞ ከዝግጅቶችም አልፎ በአዘቦት መለበስ ጀምረዋል።

ዲዛይነሯ ሥራዎቿን በማኅበራዊ ድረ-ገጽ በተለይም በፌስቡክና ቲክቶክ ታስተዋውቃለች። ታዋቂ የኦሮሞ ሞዴሎችም ሥራዎቿን በማኅበራዊ ሚዲያዎቻቸው ያስተዋውቁላት። ሥራዎቿ በተለይም በኢሬቻ በዓልና በሠርግ ወቅት ፈላጊያቸው ብዙ መሆኑን የምትናገረው ሜርሲ፣ ያም ሆኖ በአዘቦትም በዘመናዊ መልኩ የሚሠሩ የባሕል አልባሳት ተፈላጊነታቸው ጨምሯል ትላለች። በተለያየ ጊዜ ለሠርግና የተለያየ ዝግጅቶች ሲኖሩ ሰዎች የባሕል ልብስ ለብሰው መሄድ ፍላጎታቸው ጨምሯል።

በቤቷ የተወሰኑ የተዘጋጁ በዘመናዊ መልኩ የተሠሩ የባሕል አልባሳት አሉ፤ ሰው አይቶ ከወደዳቸውና ልኩ ከሆነ እነሱን ይዞ መሄድ ይችላል። ከዚያ ውጭ ግን ከዚህ ቀደም ከሠራቻቸው የሷ ፈጠራ ከሆኑ አልባሳት መካከል መርጦ ወይ በንግግር አዲስ ዲዛይን ተሠርቶለት በልኩ የማሠራት አማራጭ አለው። ከዛ ውጪም ይሄኛው ልብስ እንዲሠራልኝ እፈልጋለሁ ለሚል ደንበኛውም የፈለገው ልብስ በልኩ ታዘጋጃለች።

የባሕል አልባሳቱን ፈላጊ እየጨመረ የግብዓቶች ዋጋም እየጨመረ መምጣቱን የምትናገረው ዲዛይነሯ፤ ያም ቢሆን የአልባሳቱ ፍላጎት ከፍተኛ ነው ትላለች። ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ ውስጥ በቁጥር የነበሩት የኦሮሞ የባሕል ልብስ መሸጫዎች አሁን መበርከታቸውንም ትናገራለች።

ሜርሲ ሀገር ውስጥ ከምትሸጠው በላይ አብዛኛው አልባሳቶቿ ወደውጭ ሀገር የሚላኩ መሆኑን ትናገራለች። በውጪ ያለው የኦሮሞ ማኅበረሰብ ለስብሰባ፣ ለልደት፣ ለሃይማኖታዊ ፕሮግራሞች በጋራ አንድ አይነት በማዘዝና ተመሳሳይ በመልበስ ዲዛይኗን እንደሚጠቀሙም ትናገራች። ይህም የኦሮሞ ባሕል አልባሳትን የተሻለ ለማዘመን ያላትን ፍላጎት አሳድጎታል። ለአለባበስ ምቹና ማራኪ ሆነው በተለያዩ ቦታዎች ሲለበሱ ማየትም ትፈልጋለች። የባሕል አልባሳቱ ከኢሬቻ በዓልና ከተወሰኑ ፕሮግራሞች ውጪ እንዲለበሱ ለማድረግም ጥረቷን ቀጥላለች። ከኦሮሞ ብሔረሰብ ተወላጆች ባሻገር ሌሎችም ምርቶቿን እንዲጠቀሙም ትሻለች።

# ትዝብት/ ማረፊያ

## እያዘናጉ መለመን

**ዋሲሁን አዩሰ**

አብዛኞቻችን ልመናን የምናውቀው በአሳዛኝ ድምፀት የመላዕክትንና ቅዱሳንን ስም እየጠሩ ነው። ያው እንግዲህ ሁሉም ነገር ሲዘምን ልመናም አብሮ መዘመኑ ነው መሰለኝ አሁን አሁን የልመና ‹‹ስታይል›› እያየን ነው። በነገራችን ላይ የበለፀጉ ናቸው በሚባሉት ሀገራት ልመና በዘመናዊ የሙዚቃ መሣሪያ ታጅቦ ነው አሉ።

የሙዚቃ መሣሪያዎችን እየተጠቀሙ መለመን በእኛም ሀገር የተለመደ ነው። ለምሳሌ መገናኛ አካባቢ የሚሰሙት ባለዋሽንቶች በዕውቀቱ ሥዩም እንዳለው ለልመና ሳይሆን የባሕል ኪነት ቡድን ውድድር ነው የሚመስለው። የእነርሱ ዋሽንት ግን ለማዝናናት ሳይሆን ለማሳዘን ነው። የዋሽንት ድምፅ ልብ ውስጥ በመግባት ያሳዝናል። በጦር ሜዳ ወቅት ደግሞ ወኔን ለመሙላት ያገለግል ነበር አሉ። በነገራችን ላይ እንደ ፍቅር እስከ መቃብር ያሉ በሰው ጭንቅላት ውስጥ ‹‹ብራንድ›› የሆኑ የዋሽንት ዜማዎች ለልመና መዋላቸው በግሌ ቅር ያሰኘኛል።

አሁን አሁን እያዝናኑ መለመን በብዛት እየታየ ነው። አንዳንድ ወጣቶች ሲለምኑ፤ ልመና ይሁን ለከፋ ያምታታል። ወንዶቹ ‹‹ኧ ቆንጅት? ኧረ የሆነ ነገር ጣል አድርጊ! ኧረ ለምሳ!...›› ይላሉ። ሴቶች ‹‹ኧ ቆንጅዬው! ኧረ ውዱ! ኧረ ለምሳ ያለህን....› ይላሉ። እያዝናኑ ለመለመን ይሁን፣ ይሄኛው የተሻለ ያሳዝናል ብለው ይሁን አላውቅም።

በእርግጥ በእንዲህ አይነት መንገድ ሲለምኑ ብር ሲሰጣቸው ግን አይቼ አላውቅም። አይቼ ባለማወቄ ግን አይሰጧቸውም ብዬ አልደመድምም።

ከ8 ዓመታት በፊት ይመስለኛል ሜክሲኮ ዋቢ ሸበሌ ሆቴል ፊት ለፊት ያየሁት ልመና ነው ልመናን ከዚያ በፊት ከማውቀው አይነት የተለየ ያደረገብኝ። ከዋናው መንገድ ዳር ሆነው ሦስት ቆንጆዬ ቆንጆዬ ወጣት ሴቶች (ለዚያውም ዝንጥ ብለው የለበሱ) ወጭ ወራጁን ‹‹የእራት›› እያሉ ይለምናሉ። በመጀመሪያ እንዴት በልመና ይቀለዳል ብዬ ገረመኝ። ነገሩን ቆም ብዬ ሳስተውል ግን ሥራዬ ብለው የምራቸውን የቆሙበት ነው። ሦስቱም ሴቶች ዝንጥ ብለው የለበሱ፣ በሜካፕ የተንቆጠቆጡ ናቸው። እኔ ብቻ ሳልሆን ሌሎች ሰዎችም ግራ በመጋባት ሲያዩዋቸው የምርም ለልመና እንደቆሙ አረጋገጥኩ። አንዳንዱ እያሳቀ ያልፋቸዋል፤ በአዋቂነት ዕድሜ ላይ ያሉት ደግሞ ለምን እንደሆነ አላውቅም በጣም እየተበሳጩ ነው የሚያዩዋቸው። እንዲያውም አንዳንዶቹ ለመሳደብ ሁሉ ይቃጣቸዋል። ሴቶቹ ግን በከፍተኛ ተማፅኖ ይለምናሉ፤ ትኩረት ሳይሰጥ ያለፋቸውን ደግሞ በስድብ ይወርዱበታል። ትንሽ ፈገግ ያሰኘኝ ነገር አንድ ሰው ገላመጠን ብለው አርቀው ሲሳደቡ ልመናው እያለፋቸው ነበር።

ልጆቹ ገና በአሥራዎቹ ዕድሜ ላይ የሚገኙ ይመስላሉ። በኋላ ነገሩን ከታዘቡ ሰዎች እንደሰማሁት ተማሪዎች ሊሆኑ ይችላሉ። በሚያገኙት ገንዘብ መጠጥ ቤት ሊገቡበት ይችላሉ። ከቤተሰብ ለዚህ ታስቦ ስለማይሰጣቸው ልመና ይገባሉ። ልመናውን እንደ ነውር ሳይሆን እንደ መዝናኛ ጭምር ነው ያዩት።

ልክ የሆነ ልመና አለ ባይባልም፤ ዳሩ ግን የአንዳንዶች ደግሞ አናዳጅ ነው። የሰው ልጅ በተለያየ አጋጣሚ ችግር ይደርስበታል። ቤተሰብ ወይም ጓደኛ በሌለበት አጋጣሚ ችግር ቢደርስ ገንዘብ ብቻ ሳይሆን የተያዩ እርዳታዎች ይጠይቃል። ለምሳሌ አጉል ቦታ የስልክ ባትሪ ቢዘጋ፣ ካርድ በሌለበት ቦታ (ሞባይል ባንኪንግና ቴሌ ብር የማይጠቀም ሊሆን ይችላል) ካርድ ቢዘጋ ‹‹ተባበሩኝ›› ማለት የተለመደ ነው። በእንዲህ ዓይነቱ አጋጣሚም ልመና ነው ብሎ ማንም አይደንቀውም።

በሌላ በኩል የአካል ጉዳተኛና በዕድሜ የገፉ ሰዎች የተለያየ አይነት ርዳታ ቢጠይቁ ለማንም አይደንቅም። ሙሉ ጤነኛ ሆኖ፣ ዝንጥ ብሎ ለብሶ፣ ለዚያውም እያሾፉና እየቀለዱ መለመን ግን ምን ይሉታል?

እነዚህ ከዓመታት በፊት የምታዘባቸው የልመና አይነቶች ነበሩ። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ ሰብዓዊነትን የሚፈታተን የማዘናጋት ልመና ተጀምሯል። ይሄ ልማድ እየዳበረ ከሄደ ኢትዮጵያዊ ጨዋነትንና ሰብዓዊነትን የሚፈታተንና የሚሸረሽር ይሆናል። ነገሩ እንዲህ ነው፡፡

በመጀመሪያ የሆነ ትብብር የሚፈልጉ መስለው ያናግሩሃል። የቦታ ስም፣ የተቋም ስም ወይም የታክሲ መያዣ የሚጠይቁኝ፣ ወይም ሌላ የመረጃ ትብብር የሚጠይቁኝ መስሎህ ‹‹አቤት!›› ብለህ ጠጋ ትላለህ፤ ወይም ቆም ስትል እነርሱ ጠጋ ይሉሃል። ይህኔ ለይስሙላ ትንሽ መረጃ የሚመስል ነገር (ቦታ ሊሆን ይችላል) ከጠየቁህ በኋላ ወደ ዋናው ጉዳያቸው ይገባሉ። ዋናው ጉዳያቸው ‹‹እንዲህ ሆኜ፣ እንዲህ ሆኜ...›› በሚል ገንዘብ መጠየቅ ነው። በቀጥታ ገንዘብ ቢጠይቁ የተለመደ የልመና አይነት ስለሆነ እና በጣም ስለተደጋገመ ማንም አይሰጠንም ብለው በማሰብ ነው። እንዲህ በማዘናጋት ሲሆን ግን የተጠየቀው ሰው በይሉኝታ ሊሰጠን ይችላል ብለው በማመን ነው። አስቀድሞ መረጃ ሲጠይቁ ከቆዩ በኋላ መጠየቅ ይሉኝታ የሚያስይዝ ስለሚመስላቸው ነው። ወይም የምርም ተቸግሮ ነው የሚል ስሜት ይፈጥራል በሚል ነው፡፡

ያም ሆኖ ግን ይሄኛው ዘዴ ራሱ የተበላበት ሆኗል። ምናልባት መጀመሪያ አካባቢ የጀመሩት ሰዎች ተጠቅመውበት ሊሆን ይችላል። እየቆየ ሲሄድ ግን በብዙዎች ዘንድ ይለመድና የማያዋጣ ዘዴ ይሆናል።

የዚህ አይነት ልመና ትልቁ ችግሩ የመተባበር ባሕላችንን የሚሸረሽር መሆኑ ነው። መተማመን እንዳይኖር የሚያደርግ መሆኑ ነው። የምርም መረጃ አስፈልጓቸው የሚጠይቁ ሰዎችን የሚተባበራቸው እንዳያገኙ ማድረግ ነው። አዲስ አበባ ውስጥ ደግሞ አስቡት! ማንኛውም ሰው አዲስ አበባን ከጫፍ እስከ ጫፍ ሊያውቅ አይችልም። ቢያንስ ለተወሰኑ አካባቢዎች እንግዳ መሆኑ አይቀርም፤ ምክንያቱም የከተማ ባሕሪ ነውና የሚቀያየሩ ነገሮች፣ የሚፈርሱና የሚታደሱ ነገሮች ይኖራሉ። በዚህ ሁሉ ውስጥ ቀደም ሲል የሚያውቃቸው ምልክቶች ይጠፋሉ ወይም ይቀየራሉ፤ ስለዚህ ማንም ሰው ቢሆን ለመጠየቅ ይገደዳል። የንግድ ተቋማትም ሆኑ የመንግሥት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት በተለያየ ምክንያት አድራሻ ሊቀይሩ ይችላሉ። በዚህ ሁሉ ውስጥ ማንም ሰው መረጃ ለመጠየቅ ይገደዳል ማለት ነው፡፡

እንዲህ አይነት የሚያዘናጉ የልመና አይነቶች ግን ሰዎች እርስ በእርስ እንዲጠራጠሩ የሚያደርጉ ናቸው። ‹‹ወንድሜ! እህቴ! ጋሼ!...›› እያሉ የሚጠሩ ሰዎችን ባላዩ ባልሰማ የሚያልፋቸው ይበዛል ማለት ነው፤ ምክንያቱም በተደጋጋሚ እንደዚያ እያሉ ጠርተውት ልመና ያጋጠመው ሰው ሊሰለችና መተባበሩንም ሊተወው ይችላል። መንገደኛ ባናገረው ቁጥር ‹‹ያው ለልመና ነው!›› የሚል ስሜት ይፈጠርበታል።

እንግዲህ ለጊዜው መፍትሔ ሊሆን የሚችለው በእንዲህ አይነት ምክንያት ከሰብዓዊነታችን አለመራቅ ነው። አጭበርባሪዎች ቢያሰለቹንም መታገስና የተቸገረውንና ያልተቸገረውን ለመለየት መሞከር ነው።

# ዓለም አቀፍ

## በጀርመን ከደረሰው ጥቃት ጀርባ

በጀርመን ማግደቡርግ ከተማ ሕዝብ በተሰበሰበት የገና ገበያ ላይ በተፈጸመ የመኪና ጥቃት የ9 ዓመት ሕጻንን ጨምሮ አምስት ሰዎች ሲገደሉ ከ200 በላይ ሰዎች ቆስለዋል። አንድ ግለሰብ መኪናውን ሕዝብ በተሰበሰበበት ገበያ ላይ እንደነዳ እና በቁጥጥር ሥር እንደዋለ የጀርመን ፖሊስ አስታውቋል። ግለሰቡ ጥቃቱን ብቻውን ነው የፈጸመው ተብሏል።

የመጀመሪያው ድንገተኛ ጥሪ ሲደረግ ግለሰቡ መኪናውን የገና በዓል ገበያተኞች ላይ መንዳቱ ተገልጿል። ድንገተኛ አደጋ ነው ተብሎ የታሰበ ቢሆንም ጥቃት መሆኑ ኋላ ላይ ታውቋል። የእግረኞች መንገድ ላይ ነድቶ ሰዎቹን እንደገደላቸው ተገልጿል። መንገዱ ለአደጋ ጊዜ ጥቅም ላይ የሚውል ነው። ግለሰቡ መኪናውን በፍጥነት እየነዳ ገበያውን ደረማምሶ ሕዝብ ወደ ተሰበሰበበት ሥፍራ ሲያቀና ቪዲዮው በማኅበራዊ ሚዲያ ወጥቷል።

የዓይን እማኞች ከእግረኛ መንገድ ሮጠው በማምለጥ ራሳቸውን እንዳዳኑ ተናግረዋል። ግለሰቡ ወደ እግረኛ መንገዱ በገባበት መንገድ መልሶ መውጣቱን ፖሊስ አክሏል። ግለሰቡ ጥቁር ቢኤምደብሊው አጠገብ በቁጥጥር ሥር ሲውል ታይቷል። አጠቃላይ ክስተቱ 3 ደቂቃ የወሰደ እንደሆነ ተገልጿል።

በመኪና ጥቃቱ የ9 ዓመት ሕጻንን ጨምሮ አምስት ሰዎች ሲገደሉ ከ200 በላይ ሰዎች ቆስለዋል፡፡ ቢያንስ 41 የሚሆኑት አስጊ ሁኔታ ውስጥ ናቸው። የሞቱት ሰዎች ማንነት ገና ይፋ አልሆነም። ጥቃቱን የፈጸመው የሳዑዲ አረቢያ ዜግነት ያለው የ50 ዓመት የሥነ ልቦና ባለሙያ ታሌብ አል-አብዱልሞህሰን መሆኑ ተገልጿል። የሚኖረው ጥቃቱ ከደረሰበት ከተማ በ40 ኪሎ ሜትር ርቀት በሚገኘው በርግበርግ መሆኑ ታውቋል።

ግለሰቡ በግድያና የግድያ ሙከራ እንደሚከሰስ በዐቃቤ ሕግ ተገልጿል። ተጠርጣሪው ጥቃቱን ለምን እንደፈጸመ ግልጽ አይደለም። በ2006 ወደ ጀርመን እንደሄደና በ2016 ጥገኝነት እንዳገኘ ተገልጿል። የጀርመን የሀገር ውስጥ ሚኒስትር ናንሲ ፌሰር ተጠርጣሪው "ሙስሊም ጠል እንደሆነ በግልጽ ማየት ይቻላል" ብለዋል።

ተጠርጣሪው በማኅበራዊ ሚዲያ እና በሌሎች ድረ ገጾች ላይ እስልምናን እንደሚነቅፍ የሚጠቁሙ ጽሑፎች የተገኙ ሲሆን፤ የጀርመን መሪዎች አውሮፓን ሙስሊም ለማድረግ እየተመሳጠሩ ነው የሚል የሴራ ትንታኔም ያራምዳል። ከአንድ ዓመት በፊት ስለ ግለሰቡ ለፖሊስ ጥቆማ ቢሰጥም አስጊ መሆኑን የሚጠቁም ነገር አለማግኘታቸውን አመራሮች ተናግረዋል።

የጀርመን መራሔ መንግሥት ኦላፍ ሹልዝ "ከማግደቡርግ የሰማነው ዜና ከፍተኛ ፍርሃት ፈጥሯል" ሲሉ በኤክስ ገጻቸው ጽፈዋል። የማግደቡርግ ከተማ ካውንስለር ኖኒ ክሩግ፣ የገና ገበያው ዝግ እንደሚሆን ተናግረዋል። የገበያ አካባቢው መዘጋቱን አስታውቆ በጥቃቱ የደረሰውን ሐዘን ለመግለጽ ጥቁር ስክሪን ታይቷል። የሳዑዲ መንግሥት ለጀርመን ሕዝብ ሃዘኑን ገልጿል።

"የጀርመን ሕዝብ ከጎናችሁ ነን። በጥቃቱ ከሞቱና ከተጎዱ ቤተሰቦች ጎንም እንቆማለን። እንዲህ ያለ ጥቃትን እናወግዛለን" ብሏል የሳዑዲ መንግሥት። የዩኬ ጠቅላይ ሚኒስትር ሰር ኪር ስታርመር "በጥቃቱ አዝነናል። ለሞቱት፣ ለቆሰሉትና ጥቃቱ ጠባሳ ለጣለባቸው ሃዘናችንን እንገልጻለን" ማለታቸውን ቢቢሲ ዘግቧል።



## ዶናልድ ትራምፕ የአውሮፓ ሀገራት የአሜሪካን ነዳጅ እንዲገዙ አሳሰቡ

ዶናልድ ትራምፕ የአውሮፓ ሀገራት የአሜሪካን ነዳጅ እንዲገዙ አሳሰቡ፡፡ በመጪው ጥር ወር 2017 ዓ.ም በይፋ 47ኛው የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ሆነው ወደ ነጩ ቤተ መንግሥት የሚገቡት ዶናልድ ትራምፕ ከወዲሁ የአሜሪካ ትቅደም ፖሊሲያቸውን ተግብረዋል፡፡ ቻይናን ጨምሮ ሜክሲኮ እና ካናዳ ላይ ግብር እንደሚጨምሩ የተናገሩት ትራምፕ፤አሁን ደግሞ የአውሮፓ ኅብረትን አሳስበዋል፡፡

ትራምፕ ትሩዝ ሶሻል በተሰኘው የማህበራዊ ትስስር ገጻቸው ላይ እንዳሉት "የአውሮፓ ኅብረት የአሜሪካንን ነዳጅ በገፍ እንዲገዙ ነግሬያቸዋለሁ፤ ይህ ካልሆነ ግን ወደ አሜሪካ በሚገቡ ምርቶቻቸው ላይ የታሪፍ ጭማሪ ይጠብቃቸዋል" ብለዋል፡፡

የአውሮፓ ሀገራት ዋነኛ የነዳጅ አቅራቢ የነበረችው ሩሲያ ከዩክሬን ጋር ወደ ጦርነት መግባቷን ተከትሎ የገበያ ድርሻዋ ቀንሷል፡፡ ከሩሲያ ጥገኝነት መላቀቅ አለብኝ ያለው የአውሮፓ ኅብረት ላለፉት ሶስት ዓመታት ከአሜሪካ እና ኖርዌይ ከፍተኛ መጠን ያለው ነዳጅ ሲገዛ ቆይቷል፡፡

ከአንድ ወር በፊት በተደረገ ፕሬዚዳንታዊ ምርጫ ድል የቀናቸው ዶናልድ ትራምፕ፤ የአውሮፓ ሀገራት ተጨማሪ ነዳጅ ከአሜሪካ እንዲገዙ ጫና ማድረግ ጀምረዋል፡፡ የአውሮፓ ኅብረት በበኩሉ የዶናልድ ትራምፕን አስተያየት እንዳየው ገልጾ፤ በቀጥታ ምላሽ ከመስጠት ይልቅ ከአሜሪካ ጋር ጥሩ የንግድ ግንኙነት እንዳለው አሳውቋል፡፡

ተመራጭ ፕሬዚዳንቱ ካናዳ ወደ አሜሪካ በምትልካቸው ምርቶች ላይ የ25 በመቶ ታሪፍ ጭማሪ አደርጋለሁ ካሉ በኋላ በሀገሪቱ የፖለቲካ አለመረጋጋት የተከሰተ ሲሆን፤ ኦታዋ የተባለችውን ካላደረገች የአሜሪካ 51ኛዋ ግዛት ሆና ትቀላቀለን ብለዋል፡፡

# ስፖርት





## አትሌት ስለሺ ስህን የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት ሆኖ ተመረጠ



ብርሃን ፈይሳ

አትሌት ስለሺ ስህን የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት በመሆን እንዲያገለግል ተመርጧል። ለሁለት ቀናት በአዲስ አበባ ሲካሄድ የቆየው 28ኛው የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤም የቀድሞዋን ጀግና አትሌት መሰረት ደፋርን ጨምሮ ሌሎች ፌዴሬሽኑን ለቀጣይ አራት ዓመታት የሚመሩ አዳዲስ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት በመምረጥ ትናንት ተጠናቋል።

ፌዴሬሽኑን በፕሬዚዳንትነት ለመምራት ከስድስት ክልሎችና ከሁለት ከተማ አስተዳደሮች የቀረቡ እጩዎች በምርጫው የተፎካከሩ ሲሆን፤ ከኦሮሚያ ክልል የተወከለው አትሌት ስለሺ ስህን ከ26 ድምፅ 11ዱን በማግኘት ማሸነፍ ችሏል። በቀጣዮቹ አራት ዓመታትም የኢትዮጵያን አትሌቲክስ የሚመራ ይሆናል።

የቀድሞ የፌዴራል ማረሚያ ቤት አትሌት ስለሺ በአቴንስ እና ቤጂንግ ኦሊምፒኮች የ10ሺ ሜትር ውድድር የብር ሜዳሊያዎችን ለሀገሩ ማስመዝገቡ የሚታወስ ሲሆን፤ በፓሪስ፣ ሄልሲንኪ እና ኦሳካ የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮናዎችም 3 የብር እና አንድ የነሀስ ሜዳሊያ ማጥለቁ ይታወቃል። በተጨማሪም በመካከለኛ ርቀት 3 ሺህ ሜትር፣ በረጅም ርቀት 5 ሺህ እና 10 ሺህ ሜትር፤ በ10፣ 15 እና 20 ኪሎ ሜትር የጎዳና ላይ ሩጫዎች፤ በሀገር አቋራጭ፤ በግማሽ ማራቶንና በማራቶን ውድድሮች ከ15 ዓመታት በላይ በመወዳደር ስኬታማ ነበር።

ስለሺ ስህን የአትሌትነት ጉዞው ካበቃም በኋላም የቀድሞ ክለቡን እንዲሁም የኢትዮጵያ አትሌቶች ማህበርን በፕሬዚዳንትነት ማገልገል ችሏል። አትሌቱ ካለው የረጅም ጊዜ የአትሌቲክስ ውድድር ልምድ እና ግለሰባዊ ሥነ-ምግባር አንፃር የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ያጋጠመውን ስብራት በመጠገን ወደ ቀድሞው ገናናነቱ ይመልሰዋል ተብሎ ታምኖበታል፡፡

በጠቅላላ ጉባዔው ፍፃሜ ላይ ባለፉት ስምንት ዓመታት ፌዴሬሽኑን በፕሬዚዳንትነት በመምራት ያገለገለችው ተሰናባቿ ረዳት ኮሚሽነር ደራርቱ ቱሉን ጨምሮ አትሌቲክሱን ያገለገሉ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላትም የምስክር ወረቀት ተበርክቶላቸዋል። ዕውቅናውንም የኢፌዴሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር የስፖርት ልማት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ መኪዩ መሀመድ በመድረኩ ተገኝተው አበርክተዋል።

በተጨማሪም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስፖርት ቢሮ ከከተማው አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ጋር በመሆን እንዲሁም የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ጽሕፈት ቤት ሠራተኞች አንጋፋዋን አትሌት በስፖርቱ ላበረከተችው አስተዋጽኦ የምስጋና ስጦታ አበርክተዋል።

ኢንጂነር ጌቱ ገረመው፣ ቢንያም ምሩጽ፣ አድማሱ ሳጂ፣ ዶክተር ትዕዛዙ ሞሴ፣ አትሌት መሠረት ደፋር፣ ሳራ ሀሰን፣ አበባ ዮሴፍ እና ዶክተር ኢፍረህ መሀመድ ተመርጠዋል፡፡ በተጨማሪም ጠቅላላ ጉባኤው ከቀድሞው ሥራ አስፈጻሚ አባላቱን ጨምሮ ረዳት ኮሚሽነር ደራርቱ ቱሉ፣ ረዳት ኮሚሽነር ማርቆስ ገነቴ፣ ፎዚያ ሀሰን እና አትሌት መሠለች መልካሙን የክብር አባል በማድረግ አካቷል።

በፕሬዚዳንትነት ለመጪዎቹ አራት ዓመታት የኢትዮጵያን አትሌቲክስ እንዲመራ የተመረጠው አትሌት ስለሺ የኢትዮጵያን አትሌቲክስ ለመምራት እድሉን ስላገኘሁ አመሰግናለሁ። ከሥራ አስፈጻሚውና ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ለስፖርቱ እድገት እንሠራለን ሲልም ቃል ገብቷል፡፡